# ድሬ

እስከ የካቲት 30/2016 ዓ.ም
በሚቆየው የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድን
ምዝገባና እድሳት ተሳታፊ ይሁኑ!!
ከድንገተኛ የህክምና ወጪ ይጠበቁ!
የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ

19ኛ ዓመት | ቁጥር 863 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ | ጥር / 29 / 2016 ዓ.ም


# በድሬዳዋ አስተዳደር ከ10ሺህ 800 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

*ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሀር*

በድሬዳዋ አስተዳደር በግማሽ ዓመቱ ከ10ሺህ 800 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የአስተዳደሩ ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሀር አስታወቁ። የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት ሦስተኛ ዓመት፣ ሦስተኛ የሥራ ዘመን ሰባተኛ መደበኛ ጉባዔውን አካሂዷል።

ክቡር ከንቲባ ከድር ለጉባዔው ባቀረቡት የአፈጻጸም ሪፖርት እንዳመለከቱት በአስተዳደሩ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያው አጋማሽ በተካሄደ የሥራ ዕድል ፈጠራ እንቅስቃሴ ለዜጎች ሥራ ተፈጥሯል። በአስተዳደሩ የሥራ አጥነት ችግርንና የኑሮ ውድነትን ለማቃለል የተቀናጀ ርብርብ መደረጉንም ገልጸዋል።

በአስተዳደሩ የሚስተዋለውን የሥራ አጥነት ችግር ለማቃለል በተሰራው ሥራ በከተማ ከ8ሺህ 821 ለሚበልጡ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን፣ ከእነዚህም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸውን ተናግረዋል። በገጠርም ከ2ሺህ ለሚልቁ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፈጠሩን ከንቲባው በሪፖርታቸው አስታውቀዋል።



በተጨማሪም አስተዳደሩ በከተማው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ ባከናወናቸው ተግባራት 35 በመቶ የነበረውን የዋጋ ንረት ወደ 27 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ያስቻሉ ሥራዎች ተከናውነዋል ብለዋል። በዚህም 11ሺህ 900 ኩንታል ስኳር እና 1 ነጥብ 9 ሚሊዮን ሊትር የምግብ ዘይት ለማሰራጨት ታቅዶ 28ሺህ 600 ኩንታል ስኳርና ሁለት ሚሊዮን ሊትር የሚጠጋ ዘይት በዝቅተኛ ደረጃ ለሚኖረው ማህበረሰብ መሰራጨቱን ገልጸዋል።

በአስተዳደሩ አራት የገጠር ወረዳዎችና በከተማው ባሉ 22 ሥፍራዎች 96 የቅዳሜና እሁድ ገበያ በማቋቋም የግብርናና የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረቡን ክቡር ከንቲባ ከድር አስረድተዋል። በተጨማሪም የአስተዳደሩን ነዋሪዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚያቃልሉ 11 የልማት ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለአገልግሎት መብቃታቸውን ገልጸዋል።

በግማሽ በጀት ዓመቱ በአነስተኛና ዝቅተኛ ሥራዎች ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስርና የብድር አቅርቦት ተመቻችቷልም ብለዋል። በተጨማሪም በጤና፣ በትምህርት፣ በግብርና እንዲሁም ወጣቶችን በስፖርትና በልማት በማሳተፍ ተጠቃሚ በማድረግ በኩል አበረታች ሥራዎች መከናወናቸውን ከንቲባው አብራርተዋል።

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ከቀረበው ሪፖርት በመነሳት ለውሳኔ ሃሳብ የሚያግዙ አስተያየቶች ያቀረቡ ሲሆን፣ የምክር ቤቱ አባላትም በቀረበው ሪፖርት ላይ ተወያይተዋል። መረጃው የኢዜአ ነው።

## የኢትዮጵያና ሶማሌላንድ መግባቢያ ስምምነት በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላምና ልማት ለማረጋገጥ የጎላ ፋይዳ አለው ምሁራን







ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር የተፈራረመችው የመግባቢያ ስምምነት በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላምና ልማትን ለማረጋገጥ የሚያግዝ መሆኑን የሀርጌሳ ዩኒቨርሲቲ እና የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን ተናገሩ። ምሁራኑ ይህን የተናገሩት የሰላም ሚኒስቴር በድሬዳዋ "ሰላም ግንባታ፡ ቀጣናዊ ትስስር ለዘላቂ ልማት" በሚል መሪ ሃሳብ ባዘጋጀውና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ ስድስት ዩኒቨርሲቲዎችና የሀርጌሳ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን በተሳተፉበት መርሃ ግብር ላይ ነው።

የሀርጌሳ ዩኒቨርሲቲ መምህር አብዱላሂ መሐመድ እንዳሉት፤ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት በሰጥቶ መቀበል መርህ በመጓዝ የጋራ ዘላቂ ሰላምና ብልፅግናቸውን ለማረጋገጥ ተቀናጅተው መስራት አለባቸው። በሶማሌላንድና በኢትዮጵያ መካከል የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት በሰጥቶ መቀበል መርህ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህ ረገድ ፋርቀዳጅ ተግባር መሆኑን በማከል።

እንደ መምህር አብዱላሂ ገለፃ በቀጣናው ዘላቂ ሰላምና ልማት ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ስራዎችን ለማገዝ በድሬዳዋ የተካሄደው ውይይት የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሣይንስና ዓለምአቀፍ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

## በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በግማሽ ዓመቱ ከ2 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር በላይ ገቢ ተሰበሰበ



በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በግማሽ ዓመቱ ከተለያዩ የገቢ ርዕሶች ከ2 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር በላይ ገቢ መሰብሰብ መቻሉን የአስተዳደሩ ገቢዎች ባለስልጣን ገለጸ። የከተማ አስተዳደሩ የገቢዎች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዱልሰላም መሐመድ እንደተናገሩት፤ በዘንድሮ በጀት ዓመት አስተዳደሩ 5 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ እየሰራ ነው።

ወደ ስራ የገባውን ነጻ የንግድ ቀጠና እና የኢንዱስትሪ ፓርኩን ተከትሎ በድሬዳዋ ንግድና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ላይ መነቃቃት ተፈጥሯል ብለዋል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የሰላም ሚኒስቴር ከምስራቅ ኢትዮጵያ አጎራባች ክልሎች እና ከሶማሌላንድ እና ከጅቡቲ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር በሰላም ግንባታ ላይ ውይይት አካሄደ

❖ "ሰላም ግንባታ፣ ቀጠናዊ ትስስር ለዘላቂ ልማት" በሚል መሪ ሀሳብ የተዘጋጀ የውይይት መድረክ በድሬዳዋ ከተማ ተካሄደ፡፡

የውይይት መድረኩ በዋናነት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኢትዮጵያ በሶማሌላንድ እና በጅቡቲ መካከል ያለውን ቀጠናዊ ትስስርን እና ሁሉን አቀፍ ልማት ሰላምን ለማጠናከር የሚያስችል መድረክ መሆኑ ተገልጿል።

በውይይት መድረኩም የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የንግድ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ሀላፊ ክቡር አቶ ሀርቢ ቡህ በመክፈቻ ንግግራቸው ኢትዮጵያ ሶማሊላንድ እና ጅቡቲ በታሪክ በባህል እና በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ጥብቅ ትስስር ያላቸው ሀገራት ናቸው ብለዋል ።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋሟት ለረጅም ጊዜ የዘለቀውን ትስስር በጋራ ልማት ለማጠናከር ጎልህ ሚና እንደሚጫወቱ ተናግረዋል። ቀጠናዊ ትብብርን ለማጠናከር ና የተረጋጋ አካባቢን ለመፍጠር በቅንጅት መስራት እንደሚገባም ነው ምክትል ከንቲባው ያነሱት።

የሰላም ሚንስቴር ሚንስትር ብናልፍ አንዷለም በበኩላቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን አህጉራዊ ና ቀጠናዊ ችግሮችን በመቅረፍ የሰላም ግንባታ እና የጋራ ልማትን ለማረጋገጥ ሀላፊነታቸው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል ።



ኢትዮጵያ ለአህጉራዊ እና ቀጠናዊ ሰላም እና ልማት እየተጋች መሆኑን የገለፁት ሚንስትሩ በኢትዮጵያ በሶማሌላንድ እና ጅቡቲ መካከል የጋራ የትብብር ጉዳዮች ላይ የተቀናጀ ለመስራትም የቀጠናው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በማቀናጀት በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ ስራዎች መጀመራቸውን ገልጸዋል።

የድሬዳዋ ዩንቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ኡባህ አደም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የጋራ እሴቶችን በማጎልበት እና ወደ ጥቅም በመቀየር ረገድ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ቀጠናውን ለሁሉም ዜጎች የተመቸና የተረጋጋ የማድረግ ሀላፊነት እንዳለባቸው ጠቅሰው በዚህም የድሬዳዋ ዩንቨርሲቲ በቀጠናው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ምርምር እና መማር ማስተማር ላይ በቅንጅት እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

በውይይቱም በአፍሪካ ቀንድ ስላለው የሰላም እና የጸጥታ ጉዳይ፣የጋራ እድሎች ናስጋቶች፣ቀጠናዊ ትስስር፣የግጭት መፍቻ ስርዓቶች እና ዘላቂ ሰላም ና ልማት ግንባታ በሚል የተዘጋጁ ጥናታዊ ጹሁፍ ቀርበው ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል።

በሰላም ለማ

---

# በኢ.ፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመስክ ምልከታ ማድረግ ጀመረ

በኢ.ፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በድሬዳዋ አስተዳደር የመስክ ምልከታውን ለማድረግ ከመስተዳድሩ የስራ ኃላፊዎች ጋር የመግቢያ ውይይት በማድረግ ጀምሯል።

በውይይቱ ላይ በመገኘት ለእንግዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የንግድ የኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ የተከበሩ ሀርቢ ቡህ ያስተላለፉ ሲሆን፤ በአስተዳደሩ በንግድ፣ በኢንደስትሪ፣ በኢንቨስትመንትና በቱሪዝሙ ዘርፍ እየተሰሩ ስላሉ ስራዎችም ሰፊ ማብራሪያን ሰተዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ አሻ ያህያ በበኩላቸው ኮሚቴው በመስተዳድሩ በንግድ፣ በቱሪዝም እና በኢንቨስትመንት ዙሪያ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራትን በመስክ እንደሚመለከቱ ገልፀዋል።




የመስክ ምልከታው ዋነኛ ዓላማም በየዘርፎቹ የሚከናወኑ ተግባራት ያሉበትን የአፈፃፀም ሁኔታና ደረጃ ከመገምገም ባሻገር በአፈፃጸሙ ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉ ከሚመለከታቸውና በየደረጃው ካሉ የአመራር አካላት ጋር በመነጋገር መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑን አብራርተዋል።

ቋሚ ኮሚቴው በዛሬው የመስክ ጉብኝቱ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠናን፣ ደረቅ ወደብን እንዲሁም ምድር ባቡርን ይጎበኛል ተብሎ ይጠበቃል።

በመግቢያ ውይይቱ ላይ የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የንግድ የኢንደስትሪና የኢንቨስትመንት ቢሮ ሀላፊ የተከበሩ ሀርቢ ቡህ እንዲሁም የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ክብርት ፈቲያ አደን ጨምሮ ሌሎች የዘርፉ የስራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

በኤደን ሳሙኤል

ፎቶ:-ሙሉዓለም ደሴ

---

# የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ የመሠረታዊ ድርጅት ኮንፍረንስ አካሄደ

በኮንፍረንሱ የመሠረታዊ ድርጅቱ የ6ወር የሥራ አፈጻጸም የሥራ ክንውን ሪፖርት ቀርቧል። በሪፖርቱ በመሠረታዊ ድርጅቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ላይ ያሉ ጅምር ሥራዎችን በማጠናከር የብልፅግና ፓርቲን የመረጃ ተደራሽነት የማስፋት ስራዎችን የመሠረታዊ ድርጅቱ በማከናወን ሚናውን መወጣት እንዳለበት ተመላክቷል።

በተጓደሉ የመሠረታዊ ድርጅትን አባላትም በኮንፍረሱ ተተክተዋል። በኮንፍረሱ ላይ የተገኙት የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ የሥራ መመሪያ የሰጡ ሲሆን ኮንፍረንሱ ባለ4 ነጥብ የአቋም መግለጫ በማሰማት ተጠናቋል።

በሄኖክ ይልማ



## ርዕሰ - አንቀጽ

# ሕግና ሥርዓት ሲጠፋ

በሕግና በሥርዓት የማይተዳደር አገር የሥርዓተ አልበኞች መፈንጫ ይሆናል፡፡ በተለይ አገር የፖለቲካ ሽግግር ውስጥ ስትሆን ሕግና ሥርዓት ካልኖረ ለትርምስ በር ይከፈታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ሥፍራዎች የሚሰሙት የግጭት፣ የሞትና የውድመት ዜናዎች እረፍት ይነሳሉ፡፡

ለዓመታት የተዘጉ እስር ቤቶች ተከፍተው እስረኞች ሲለቀቁ፣ በከባድ የጭቆና ቀንበር ውስጥ የቆዩ ሰዎች ዘና ሲሉ፣ በዝምታ ተሸብበው የነበሩ አንደበቶች መናገር ሲጀምሩ፣ ስለፍትሕና ነፃነት ሲጮኹ የነበሩ ተስፋ ሲሰንቁና አገርን ቀውስ ውስጥ የሚከቱ አጓጉል ድርጊቶች አደብ ሲገዙ ለውጥን ማስተናገድ አለመቻል ያስተዛዝባል፡፡

የመከራ ቀንበር ተጭኖብን ቆይቷል የሚሉ ወገኖችም ሆኑ፣ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ያለፉ ሰዎች ለውጥን ማስተናገድ አቅቷቸው በየቦታው ሞትና ውድመት ሲሰማ ለምን ተብሎ መጠየቅ አለበት፡፡ የአገርን ሰላምና የሕዝብን ደኅንነት ችግር ውስጥ የሚከቱ ብሔር ተኮር ጥቃቶች ሲፈጸሙ እንዳላዩ ሆኖ ማለፍ አይቻልም፡፡ ሕግና ሥርዓት እየተናዱ በየቦታው ጉልበተኞችና እንዳሻቸው አዳሪዎች ሲፈነጩ ዝም ማለት፣ ራስን ለሌላ ዙር ቀውስ ማዘጋጀት እንደሆነ ሊታሰብበት ይገባል፡፡

በአንድ ወቅት አንድ የክልል ርዕሰ መስተዳድር ‹‹የጭቆና ቀንበርን መሸከም የቻለ ጫንቃችን ነፃነትን ማስተናገድ እንዴት ያቅተዋል?›› እንዳሉት፣ ምራቃቸውን የዋጡ አንጋፋዎች በእየአካባቢያቸው ይኼንን መልዕክት የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው፡፡ በረባ ባልረባው ምክንያት የሚፈጠር የግለሰብ ፀብ ሳይቀር የብሔር ገጽታ እየተላበሰ በየቀኑ የግድያ ዜና መስማት ያሳምማል፡፡

ለውጡን በይቅር ባይነትና በፍቅር መቀበላቸውን በአደባባይ የሚገልጹ ሰዎች ሳይቀሩ፣ ጥላቻና ቂማቸውን በተለያዩ መንገዶች ሲናገሩ ይሰማሉ፡፡ እነሱን እንደ አርዓያ የሚከተሉ ወጣቶች ደግሞ አንድ ነገር ሲፈጠር ሕገ-ወጥ ድርጊት ውስጥ ይሰማራሉ፡፡

ፀጥታ ማስከበር የሚገባቸው ተቋማትም ሆኑ አመራሮች ከሕገ-ወጦች ጋር መፋጠጥ ስለማይፈልጉ አሳዛኝ ጉዳቶች እየደረሱ ነው፡፡ ሕግ ማስከበር የሚገባቸው አካላት ሳይቀሩ ሲፍረከረኩ ሕግና ሥርዓት እንዴት ይኖራል? ይኼ ችግር በጊዜ እልባት ካልተደረገለት የአገር ጉዳይ ያሳስባል፡፡ የሚመለከታቸው ሁሉ አፅንኦት ሊሰጡት ይገባል፡፡

የአገሪቱ የፖለቲካ ባህል እጅግ በጣም ከመበላሸቱ የተነሳ፣ የቂምና የቁርሾ ሕመም አገር እንደሚያጠፋ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ አንዱ ሌላውን ለማጥፋትና የበላይነት ለማግኘት የሚደረገው ሩጫ የፖለቲካው ደዌ ማሳያ ነው፡፡ አብሮ መብላት እንጂ አብሮ መሥራት እርም በሆነበት ልማዳዊ አኗኗር ላይ፣ ብልሹው ፖለቲካ ተጨምሮበት አገርና ሕዝብ ብዙ መከራ አይተዋል፡፡

ለአገሩ ላቡን ጠብ አድርጎ የሠራ ትሁት ሰው በአደባባይ በጥይት በሚገደልበት በዚህ ዘመን፣ መረጃና ማስረጃ ተጠናቅሮ በይፋ የገዳዩ ማንነት ሳይረጋገጥ የደም ፍላት ዕርምጃ በተገኘው ላይ ለመውሰድ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚል በበዛበት በዚህ ጊዜ፣ ኧረ ይኼ ነገር ለአገር መዘዝ አለው የሚል የሽማግሌ ድምፅ በማይሰማበት በዚህ ወቅት፣ የሕግ የበላይነት ልዕልና ካላገኘ ጦሱ የሚተርፈው ለሕዝብ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

ከታሪክ እንደምንማረው ማንኛውም ክስተት ሁለት ገጽታዎች አሉት፡፡ አንደኛው የበላይነት ያገኘው ከማንም የበለጠ የሚደመጥበት፣ ሁለተኛው ተሸናፊው ወይም ቀን ዘንበል ያለበት ድምፀ ሰላላ መሆኑን ነው፡፡ ይኼን ጊዜ ታዲያ ፍትሕ ያስፈልጋል፡፡ ፍትሕ የሚሰፍነው ደግሞ የሕግ የበላይነት ሲረጋገጥ ነው፡፡ ሕግና ሥርዓት መኖሩ የሚበጀውም ሕገ-ወጥነትን ለመከላከል ይሆናል ማለት ነው፡፡

የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግሥታት ሕግና ሥርዓት ሲያስከብሩ የዜጎች ነፃነትና መብት ዋስትና ያገኛሉ፡፡ ማንም ሰው የመሰለውን ሐሳብ በነፃነት መግለጽ አለበት፡፡ የፈለገውን የመደገፍ ያልፈለገውን የመቃወም መብቱም እንዲሁ፡፡ በመላ አገሪቱ በፈለገው ሥፍራ የመኖር፣ የመዘዋወር፣ የመሥራትና ሀብት የማፍራት መብት በሕግ የተረጋገጠለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣ በማንነቱም ሆነ በእምነቱ ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስበት የሚከላከልለት ሕግ ብቻ መሆን አለበት፡፡

ዋስትና የሰጠውን ሕግ ተማምኖ በመላ አገሪቱ ተሠራጭቶ የሚኖር ኢትዮጵያዊ በሕገወጦች ምክንያት ከቀዬው ሲፈናቀል፣ ሲዘረፍ፣ ሲገደልና ሲሳደድ ማየት አዲስ ነገር አይደለም፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተገድለው በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የተፈናቀሉበትን የቅርብ ጊዜ ክስተት ብቻ ማውሳት ተገቢ ነው፡፡

መብራት ለምን ጠፋብን ተብሎ ኢትዮጵያዊያን በገዛ አገራቸው በማይመለከታቸው ጉዳይ ሲገደሉ ወዴት እያመራን ነው መባል አለበት፡፡ አንድ ችግር ባጋጠመ ቁጥር የገዛ ወገንን የጥቃት ሰለባ ማድረግ መዘዙ የከፋ ነው፡፡ ሕግና ሥርዓት ካልተከበረ ከፊታችን ከፍ ያለ አደጋ ይጠብቀናል፡፡

አስተዋዩና ጨዋው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ነገሮችን እየታዘበ ነው፡፡ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለሚመለከታቸው አካላት የሚናገረው ሰላምና መረጋጋትን በተመለከተ ነው፡፡ ሰላም ከሌለ ልማትና ዕድገት አይታሰቡም፡፡ ሰላም ከሌለ እንኳን ልማት አገርም አትኖርም፡፡

ይህ ኩሩና አስተዋይ ሕዝብ ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲቀባበል የዘለቀው አብሮ በሰላም በመኖር ነው፡፡ ከዚያም አልፎ ተርፎ ማንነትና እምነት ሳይገድቡት ተጋብቶና ተዋልዶ ትስስር ፈጥሯል፡፡ ይህ የሚያኮራ የጋራ እሴቱ በዚህ ዘመን በሕገ-ወጦች ሲደፈር በሕግ መባል አለበት፡፡ የገዛ ወገኑን በአደባባይ ገድሎ የሚደበቀውም ሆነ ነውሩን መሸፈን ያልቻለው በሕግ ሊዳኝ ይገባዋል፡፡

መንግሥት ሕዝብን የማገልገል ኃላፊነቱ የሚጀምረው ደኅንነቱን በመጠበቅ ነው፡፡ የፀጥታና የፍትሕ አካላትም ወንጀል ሲፈጸም ተከታትሎ በመያዝ ተገቢው ፍትሕ እንዲሰፍን የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ሕገ-ወጥነት በሕጋዊነት ላይ የበላይነት እያገኘ ሲሄድ ውጤቱ ውድመት ነው፡፡

አገር የለውጥ ማዕበል ውስጥ ሆና ከአገር ቤት እስከ ሰሜን አሜሪካ ድረስ የአንድነት መዝሙር እየተሰማ፣ በተቃራኒው አገርን የሚያፈራርሱ ሕገወጥ ድርጊቶችን በቸልታ ማለፍ ለማንም አይጠቅምም፡፡

## አጀንዳ

# የዋጋ ንረቱ መፍትሄ ይበጅለት !

ከዚህ ቀደም በኮሮና ወረርሽኝ፣ በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶች፣ በሰሜን ኢትዮጵያ አውዳሚ ጦርነት፣ አሁን ደግሞ በአማራ ክልል እየተካሄደ ባለው ግጭት ሳቢያ የምግብና የምግብ ነክ ምርቶች፣ የግንባታ ዕቃዎችና ሌሎች ሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ በየቀኑ ወደ ላይ እያሻቀበ ነው፡፡ ከቅርብ ቀናት ወዲህ ደግሞ በጤፍና በሌሎች የምግብ ምርቶች ላይ እየታየ ያለው አስደንጋጭ የዋጋ ንረት መግቻ ካልተደረገለት፣ የዜጎች ሕይወት ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ ሰብዓዊ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡

ለዋጋ ንረት መከሰት በመሠረታዊነት ከሚጠቀሰው የአቅርቦትና የፍላጎት አለመጣጠም በተጨማሪ፣ ወትሮም ሥርዓተ አልባ የሆነው የግብይት ሥርዓት ውስጥ የሚስተዋለው ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ የዜጎችን ሕይወት እያመሰቃቀለ ነው፡፡ ይህ ችግር ፍቱን የሆነ የፖሊሲ ውሳኔ የሚያስፈልገው ሲሆን፣ በበሳል የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ግራና ቀኙ በሚገባ ተጠንቶ ለመፍትሔ የሚረዳ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ለማስገንዘብ እንደተሞከረው የፖሊሲ ውሳኔ ላይ ከመድረስ በፊት፣ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ምክረ ሐሳብ ስለመገኘቱ ማረጋገጫ ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅርቡ ባወጣው የገንዘብ ፖሊሲ መግለጫ፣ በኢትዮጵያ የዋጋ ንረት ለበርካታ ዓመታት የማክሮ ኢኮኖሚ ተግዳሮቶች መካከል አንዱ መሆኑን ገልጿል፡፡ ባለፉት አሥር ዓመታት የዋጋ ንረት በአማካይ የ16 በመቶ ዕድገት ማሳየቱን፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት የተስተዋለው ደግሞ ከዚህ አማካይ የዘለለና ከተጠበቀው በላይ ክስተት መሆኑን አስታውቋል፡፡ ብሔራዊ ባንክ እንዳለው በማክሮ ኢኮኖሚውም ላይ ሆነ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ዜጎች የዕለት ተዕለት ሕይወት ላይ ከሚያሳድረው ተፅዕኖ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ጉዳት አለው፡፡

የዋጋ ንረት ቋሚ ገቢ ያላቸውን ሰዎች ትክክለኛ ገቢ እንደሚቀንስ፣ በድህነት የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እንደሚጎዳ፣ ንረቱ በቆየ ቁጥር ሥር የሰደደ ሥጋት እንደሚፈጥር፣ የዋጋ ንረት ይኖራል የሚለው ዕሳቤ በራሱ አባባሽ ሁኔታ ስለሚፈጥር በጊዜ መገታት እንዳለበት ብሔራዊ ባንክ በመግለጫው አክሏል፡፡ ለዘለቄታዊ መፍትሔ የቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊነት፣ የአቅርቦት ማሻሻያ ዕርምጃዎች፣ መዋቅራዊ ዕርምጃዎች፣ የፊስካል ፖሊሲና የብሔራዊ ባንክ ልዩ ሚና በማለት በረዥም ጊዜና በአጭር ጊዜ የዋጋ ንረትን ለማርገብ የሚረዱ ያላቸውን ውሳኔዎች አብራርቷል፡፡

እንደሚታወቀው ለዋጋ ንረት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ብሔራዊ ባንክ በመግለጫው ለረዥም ጊዜ የቆየውን የዋጋ ንረት ችግር ለመቅረፍ የብዙ ወገኖችና ዘርፎች ቅንጅትና ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህም ሲባል በመስኩ አንቱ የተባሉ ባለሙያዎችን ተሳትፎ እንዲኖር ከማድረግ በተጨማሪ፣ በተለይ በመንግሥታዊ መዋቅሩ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካላት አቅምና የአመራር ችሎታም መፈተሽ አለበት፡፡

የግብይት ሥርዓቱን ፈር ማስያዝ ያቃታቸው የዘርፉ መዋቅሮችና አመራሮች ጉዳይ በቅጡ ሳይፈተሽ፣ የእነሱ መቀናጀትና የመሳተፍ ጉዳይ ከፈረሱ ጋሪውን እንደማስቀደም ነው የሚሆነው፡፡ በምግብ እህሎችና በፍጆታ ዕቃዎች አቅርቦትና ሥርጭት ውስጥ የተሰገሰጉ ሕገወጦች፣ የግብይት ሥርዓቱን እንደፈለጉ ሲፈነጩበት ማንም ሊያስቆማቸው ያልቻለው መንግሥታዊ መዋቅሩ ውስጥ በሚታየው ዳተኝነት ምክንያት ነው፡፡ ይህ ዳተኝነት በሁለት ምክንያቶች የሚታይ ሲሆን፣ አንደኛው የጥቅም ተጋሪ በመሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በአቅም አልባነት ነው፡፡ በዚህ መሀል ግን የግብይት ሥርዓቱ ለሕገወጦች መፈንጫ ለሸማቾች ደግሞ ሲኦል ሊሆን ችሏል፡፡

የምግብ አቅርቦትን ለማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ወሳኝ ነገር መሆኑን በማመን የሚታረስ መሬት መጠን መጨመር፣ የመስኖ እርሻ ማስፋፋት፣ የኩታ ገጠም እርሻ ማበረታታት፣ የሜካናይዜሽን እርሻ ማስፋፋት፣ ቆላማ አካባቢዎችን እርሻ ማለማመድ፣ በስፋት ለፍጆታ የሚውሉ እንደ ስንዴና አትክልትና ፍራፍሬ ያሉ ሰብሎችን ምርታማነት መጨመርና የመሳሰሉ ፍላጎቶችና ዕቅዶች መኖራቸው መልካም ነው፡፡ እንዲሁም በሌሎች ሸቀጦችና አገልግሎቶች፣ በሲሚንቶ፣ በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ፣ በትራንስፖርትና በመሳሰሉ ዘርፎች ያለውን የአቅርቦት ችግር ለመቅረፍ መታሰቡም ጥሩ ነው፡፡

ከእነዚህ ፍላጎቶች ጎን ለጎን ምክንያታዊ ያልሆኑ የዋጋ ጭማሪዎችን በመግታት መረጋጋት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በአማራ ክልል የተከሰተው ግጭት በሰላማዊ መንገድ ተቋጭቶ፣ የሰዎችና የምርቶች አቅርቦት እንደገና እንዲጀመር ጠንክሮ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ግጭቱ በተራዘመ መጠን የምርቶች አቅርቦት እየተስተጓጎለ የሚፈጠረው እጥረት የዋጋ ንረቱን ያባብሰዋል፡፡ ከሌሎች አካባቢዎች የሚገቡ ምርቶች ለሸማቾች በቂ ስለማይሆኑ፣ ከእጅ ወደ አፍ የሆነውን የከተማ ነዋሪዎች ኑሮ ያመሰቃቅሉታል፡፡ ሕዝባችን ገቢው ሳይጨምር በከባድ የዋጋ ንረት እየተመታ መቀጠል አይችልም፡፡

መንግሥት ከዚህ ቀደም ባጋጠሙ ኮቪድ፣ ግጭትና ድርቅ ሳቢያ በደረሱበት ጫናዎች ምክንያት የወጪ ፍላጎቱ መጨመሩ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ክስተቶች የገቢ ዕድገት በመቀነሳቸው ሳቢያ ከፍተኛ የፊስካል ተግዳሮት ፈጥረው የመንግሥት ገቢ ጉድለት በከፍተኛ መጠን መጨመሩም አይዘነጋም፡፡ የውጭ ብድርና ዕርዳታ መጠን በመቀነሱም መንግሥት ፊቱን ወደ አገር ውስጥ የብድር ምንጮች፣ በተለይም ወደ ብሔራዊ ባንክ አዙሮ ወጪውን ለመሸፈን መገደዱም እንዲሁ፡፡

በተያዘው የ2016 በጀት ዓመት ግን የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ሲባል መርሐዊ አቋም በመያዝ፣ ወጪው በእጅጉ መገደቡ በብሔራዊ ባንክ አማካይነት መገለጹ አይረሳም፡፡ መንግሥት በዚህ ደረጃ ወጪዬን በመቀነስ የበጀት ጉድለቱን እቀንሳለሁ ሲል፣ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ፕሮጀክቶቹ መካከል ግን ሰብዓዊ ፍጡራንን መዘንጋት እንደሌለበት ማሳሰብ ያስፈልጋል፡፡ ሰሞኑን እየታየ ያለው የምግብ እህሎች ዋጋ ንረትን በተመለከተ፣ መንግሥት የሚፈለግበትን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ የተዝረከረከው የግብይት ሥርዓት ጥቂቶችን እያደለበ ብዙኃኑን እያስራበ ነው፡፡ የሰሞኑ ተከታታይ የዋጋ ንረት በቁርጠኛ አመራር መርገብ ካልቻለ መዘዙ የከፋ ነው፡፡

ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደተሞከረው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በርካታ ችግሮች አሉበት፡፡ ኢትዮጵያ ሰላም አግኝታ በአዋጭ ፖሊሲ የተደገፈ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ካልተፈጠረ በስተቀር፣ አሁን ባለው ሁኔታ ወደኋላ እንጂ ወደፊት አንዲት ጋት መራመድ አይቻልም፡፡ በመላ አገሪቱ ሰዎችና ምርቶች በሚፈለገው ልክ ካልተዘዋወሩ የምርቶች አቅርቦት ይገታል፡፡ አቅርቦት ሲያንስ ደግሞ ፍላጎት በጣም ይጨምራል፡፡ በዚህ ላይ የግብይት ሥርዓቱ በወጉ ስለማይመራ ሸማቾች ምክንያታዊ ላልሆነ የዋጋ ንረት ይዳረጋሉ፡፡ መንግሥት ገበያው ውስጥ የሚረጨውን ገንዘብ ለመቀነስ ቃል ሲገባ በተግባር መታየት ይኖርበታል፡፡

በአገሪቱ በርካታ ሥፍራዎች የሰዎችና የምርቶች ዝውውር ሲገታ፣ ሊከተል የሚችለው እጥረት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች መጠን ሲቀንስ የዋጋ ጭማሪ እንደሚኖር ማንም ይረዳዋል፡፡ ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ንረትን በ2016 በጀት ዓመት ሰኔ መጨረሻ 20 በመቶ፣ በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ደግሞ ከ10 በመቶ በታች ለማውረድ ይሠራል ማለቱ ይታወሳል፡፡ ነገር ግን ሰሞኑን እየታየ ካለው አስፈሪ የዋጋ ንረት ጋር አብሮ የሚሄድ አይመስልም፡፡ የዋጋ ንረቱ በጥናት ላይ የተመሠረተ ልጓም ይበጅለት!

የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ በየሳምንቱ የሚታተም **ሚያዚያ 21/1996 ዓ.ም** ተጀመረ

ረቡዕ -ጥር / 29 / 2016 ዓ.ም

ድሬ ጋዜጣ

**አዘጋጆች**
በድሉ ኃይሌ
ማቲያስ እንዳለ
እስክንድር ኡስማን

**ፎቶ ግራፈር**
ሰላም አበበ

**ዋና አዘጋጅ**
ሔለን ሽጉጤ
( 09 20 26 49 55 )

**ሌይአውት ዲዛይን**
ሰማን ሙስጠፋ

**የኮምፒዩተር ፅሁፍ**
አለም አስጨናቂ

ስልክ - 025 111 6065
ፋክስ - 025 111 4972 ፖ.ሳ.ቁ 370
ኢ-ሜይል - Info pubbure@yahoo.com
ዌብሳይት - www.direcomm.gov.et
ፌስቡክ - Dire Dawa Geovernement Communication Affairs Bureau (@DDGCAB)

# ከሰው ጋር...

በስንታየሁ እንግዳ

ሰውና ተፈጥሮ ብቻቸውን ተፋጠው ኖረው ያውቀሉ፡፡ ያኔ ሰው ለተፈጥሮ ተፈጥሮ ደግሞ ለሰው አንዱ ለአንዱ እየተሳሰቡ አንደኛቸው አንዳቸውን እየተንከባከቡ ከላይ በፈጣሪያቸው የሚሰጣቸውን ትእዛዝ እየተገበሩ ሁለቱም ወደ መኖር ላመጣቸው አምጪቸው የልባቸውን እንደየ ቋንቋቸው እየነገሩና የሚባሉትንም እየሰሙ ለስንት ዓመታት እንደሆነ እርግጡን መናገር ባልችልም ብቻ ያለ አንዳች ተቃርኖ ተኗኑረዋል ሰውና ተፈጥሮ፡፡

ያ ሰው አንዱ አዳም መሆኑን የሀይማኖት አባቶች ብቻ ሳይሆኑ መፅሐፍቶቻቸውም ያወሳሉ፡፡ ግን ደግሞ በሆነ ወቅት ላይ ሰውና ተፈጥሮን ያለተቀናቃኝ ለብቻቸው የሚኖሩበትን መንገድ የሚያሰናክል ሌላ ተቀናቃኝ እነሱኑ ከፈጠረው ከፈጣሪያቸው ዘንድ ተቸራቸው፡፡

ለካ ጫካው ምን ቢያምር፤ ወንዝና ፏፏቴዎች ድምፃቸውና ኩልል ያለው መልካቸው ልብን ቢማርክ፤ የአበቦች ሽታ በአፍንጫ ገብቶ መአዛቸው እስከ ውስጠኛው ማንነታችን ሰተት ብሎ እየገባ ቢያውድ፤ ተቀጥፎና ተቆፍሮ የሚበላው የምድር ውስጥና ገፀ-በረከቷ ሞልቶ ቢትረፈረፍ፤ የመስኩ ሳርና የምድሩ አቀማመጥ ለአዳም ባዶ እግሮች አሁን ከምንለብሰው የዓለም ውዱ ጫማ በተሻለ ምቾት ቢሰጡት፤ አናብስትና ሌሎች አራዊቶች በአዕዋፍ ዜማ እያጀቡ ለአዳም መኖሪያ እጥፍ ድርብ ውበት ቢሆኑት አዳም ግን ለብቻው መሆን አልተዋጠለትም መሰለኝ ‹‹ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም›› ብሎ ሰው ብቻውን እንዳይሆን ከገዛ ከራሱ ከአዳም አጥንት እንሰቷን ሄዋንን እነሆኝ አለው፡፡

ያኔ ተጀመረ፡፡

ምኑ? አትሉኝም ሰው ያለሰው መኖር አለመቻሉን የሚያሳብቁ ምልክቶች፡፡ መፅሐፍ እንደሚለው ሰይጣን በእባብ አምሳል ያሳታት ጊዜ ከሄዋን ጋር አብሯት ነበር፡፡ አዳም እሷ የሰጠከኝ ሴት አሳተችኝ ያለ ጊዜም ሄዋን አብራው ነበረች፡፡ እንዴት ጣቱን ወደኔ ይጠቁማል ብላ ጥላው አልፈረጠጠችም፡፡ ሁለቱም የሚያመካኙቱ ቢኖራቸውም አንዳቸው ከአንዳቸው ሊነጠሉ ግን አልቻሉም፡፡

እርቃናቸውን ለመሸፈን አብረው መፍትሄ ፈልገዋል፤ የተጣለባቸውን ቅጣት አብረው ተቀብለው አብረው ዳገት ቁልቁለቱን ወርደዋል ወጥተዋል፡፡ አብረው ወልደው ከብደዋል ደግሞም ቀድሞ ሳይዘሩ ሳያጭዱ እንደበሉት ሁሉ አብረው ቆፍረው የአፋቸውን ውዳቂ ፍሬ ተክለው ተመግበዋል፡፡ እሷ ያለሱ እሱ ደግሞ ያለ እሷ መኖር አልሆነላቸውም፡፡

ዘመን ዘመናትን ወልዶ በአዳምና በሄዋን ልጆችና የልጅ ልጆችም ልክ እንደነሱ ሁሉ አንዳቸው ከአንዳቸው መለየት አቅቷቸው በዘመን ላይ ሰልጥነው ከነ ፍቅርና ፀባቸው እየተዋደዱና እየተጣሉም ቢሆን አብረው ዘመን ተቆጥሮላቸዋል፡፡ ደግሞም ዘመንን ለኛ ለዛሬዎቹ አስቀርተውልን ሰውና ሰው አብሮ መኖርን እንደ አንዱ የህይወቱ ክፍል ተቀብሎ በማፅደቅ እሱና አብሮ መኖር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ሆነው ያኔና ትናንትናም ነበሩ፤ ዛሬንም አብረው እየኖሩ ነው ነገንም ይኖራሉ፡፡ ከአዳም ፍጠረት ጀምሮ ያለው ነገር ይሄው ነው፡፡ ያለ ሰው ምንም መሆን አይቻለም፡፡

ያ ለሰው፡፡

ቅድመ አያቶቻችንና አያቶቻችን እንዲሁም እናት አባቶቻችን እንደገናም እኛም የዛሬዎቹ አብረን ለመኖር ስንል ያልቆፈርነው ጉድጓድ ያልካብነው ካብ የለም፡፡ እናት አባቶቻችን ከጓዳ ዕድር/አፎሻ/እስከ ቀበሌ መረዳጃ ትላልቅ ዕድሮች/አፎሻዎች/፤ ከቤተሰብ ጉባኤ እስከ አገር ልጆች ማህበራት ወዘተ. ሰው ከሰው ጋር አብሮ ለመኖር የዘረጋቸው የመገናኛና የመረዳጃ ወይም አንዱ የአንዱን ጀርባ ማከኪያ መንገዶች ናቸው፡፡

‹‹ደሞ ከሰው ጋር የምን መኖር›› ብሎ እራሱን ከሰው መካከል ለነጠለ ብቸኝነት ናፋቂ ብቸንነትን መምረጡን እና ከሰው መለየቱን አንዱ ለሌላ ‹‹ወቸው ጉድ አይገርምም?›› እያለና እያዳነቀ የሚያወራለት ሰው ያስፈልገዋል፡፡ ያለሰው አይደለም ብቸኝትን መምረጣችን እራሳችንን ማጥፋታችን እንኳን አይታወቅልንም፡፡ ስለዚህ ያለ ሰው ምንም ነን፡፡

እኛን በአራቱም አቅጣጫ ያለን ኢትዮጲያዊያንን ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጠናወተን ነገር አለ፡፡ ‹‹እኔ ብቻ›› የምትል አባዜ ይህ ክፉና ወደ ማንወጣው አዘቅት እየሳበን ያለው የ እኔ ብቻ አባዜያችን ተለክቶ ያልተሰጠንን ምድር እያስለካን፤ ተሰፍሮ ያልተሰጠንን አፈር እያሰፈረን፤ ቆጥረን ያልተረከብነውን ጋራና ሸንተረር እያስቆጠረን የኔነትን እያበዛና እኛነትን እያኮሰመነ ከቀደመው የአብሮነት ምርጡ ተሞክሮዋችን ጋር ተቃርኖን እየፈጠረ ግለኞች እያደረገን ነው፡፡

ኢትዮጲያዊነት ውበት ነው፤ ውበት ደግሞ ውበትነቱ የሚታወቀው አድናቂ ሌላ አካል ሲኖር ነው፤ ኢትዮጲያዊነት ፍቅር ነው፤ ፍቅርም ደግሞ የሚገለጠው የሚፈቀር ሲኖር ነው፤ ኢትዮጲያዊነት ጀግንነት ነው፤ ጀግንነትም ተዋግተን አሊያም ታግለን የምናሸንፈው ሲገጥመን ነው የሚታወቀውና የሚደነቀው፡፡

ሰው ጀግና ነው፤ ሰው አፍቃሪ ነው፤ ሰው ያዝናል ደግሞም ሰው ይደሰታል፤ ሰው ይነግዳል ነግዶም ያተርፋል፤ ሰው ሰው መሆን ያለበትን ሁሉ ይሆናል ግን ደግሞ ሰው መሆን ያለበትን ለመሆን ያለ ሰው አይቻለውም፡፡ የሠራሁት በጎም ይሁን መጥፎ ሥራ ገኖም ይሁን በደብዛዘው የሚገለጠው ባንተ በወንድሜና ባንቺ በእህቴ ነው ምክኒያቱም ያደረኩትን ሁሉ የማደርገው ባንተና ባንቺ መካከል ሆኜ ስለሆነ ነው በሰውኛ ሚዛን ተለክቶ በጎና መጥፎ ተብሎ የተለየው፡፡ እንጂማ ያደረኩትን የማደርገው ከሰው ተነጥዬ ቢሆን ለበጎነቱ እና ለመጥፎነቱ ማረጋገጫ ልኬት ባላገኝሁ ነበር፡፡ ስለዚህ ሰው ሆነክ የተፈጠርከው ከሰው ጋር እንድትኖር እንጂ እኔነትን እያቀነቀንክ፤ ጥላቻን እየዘራክ፤ ከኔ በቀር ላሳር እያልክ አግላይ ሆነክ ያለ ሰው ትኖር ዘንድ አይደለም፡፡

ሮጠክ አንደኛ የወጣከው ከራስክ ጋር ተወዳድረክ አይደለም፤ ነግደክ ያተረፍከው ከጥላክ ጋርም አይደለም፤ አይተክ የወደድከው መናፍስትን አይደለም፤ ተናግረክ አንደበተ ርቱዕ በመሆንክ ያጨበጨቡልክ አራዊት አይደሉም ወዘተ. ወዘተ. ወዘተ. ያደረከውን ሁሉ ያደረከውና የሆንከውን ሁሉ የሆንከው ዛሬ ክልሌ፣ ግዛቴ፣ ድንበሬ ምናም እያልክ ጦር የምትወረውርበትና ስለት የምትሰነዝርበት ሰው ከተባለው አምሳያክ ጋር ነው፡፡

እናም ያለሰው ምንም ነክ፡፡ እንደውም ምንም ብቻ ሳትሆን ንክ ነክ፡፡ እስቲ በሞቴ አዳም ግዛቱ ከየት እስከ የት ነበር? ሄዋን ምድሯን አስምሮ የሰጣትና ካርታሽ ከዚህ እዛ ድረስ ነው ብሎ የገደበላት ማነው? ማንም፡፡ እግራቸው እስከቻለው ይሄዳሉ፤ ዐይናቸው እስከቻለው ያያሉ፤ ያሰኛቸው ቦታ ያድራሉ ይውላሉ፡፡

ታዲያ በሞቴ ተፈጥሮ በተሰጠን ነገር እንደፈጣሪ የሚያደርገንና ምድርን እኛ ጠፍጥፈን እዚህ ያደረስናት አስገኚዎቿ ይመስል አንዱን ውጣ አንዱን ግባ፤ አንተ የዐይንህ ቀለም አለማረኝምና ከፊቴ ወግድ ቅብርጥሶ ምንትሶ በሚሉና ጆሮን ጭው በሚያደርጉ ሰበብ አልባ ምክኒያቶች ተሞልተን እና በርካሽ የ‹‹እኔ ብቻ›› ክፉ መንፈስ ተተብትበን እኛ ብቻ በቂ በሚል እሳቤ ያልነኩንን እየነካን፤ ያልገፉን እየገፋን፤ የወደዱንን እየጠላንና ያልተጣሉንን እየተጣላን እስከ ደም ማፍሰስ እንደርስ ዘንድ እኛ ማነን? እስቲ ከቆየው የአበው የኑሮ ተሞክሮ ቀምሮና የራሱንም የትናንት የኑሮ አብሮነት ደምሮ ያለሰው መኖር የቻለ ሰው እስቲ ጣቱን ያውጣና እኔ አለሁ ይበለኝ፡፡

እስቲ ያለ ሰው በዘሩና በጎሳው ተወስኖ በተለይ እዚህች የአብሮ መኖር ተምሳሌ በሆነች ሀገረ ኢትዮጲያ ላይ የራሱን ደሴት ሰርቶ አትድረሱብኝ አልደርስባችም ብሎ ዘመኑን የገፋ ማነው? ማነው እሱ ዘሩ ከአጥንተ ከባዶቹ ነው ተብሎና እንደ ዘር እህል ከፍ ተደርጎ ተሰቅሎ ነገር ግን ያለሰው መኖር የቻለ? ማነው ለደሃ ሸጦ ሀብት ያላካበተ? እንዴ! የጨረስኩ አዋቂ ነኝ ብትል እንኳን አዋቂነትክ የታወቀልክ ባላዋቂዎች መካከል ስለሆንክ እኮ ነው ።

ወዳጄ የሚያምርብን ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር ደግሞ ሰጪና ተቀባይ ይፈልጋል ለዚህ ነው ለመውደድም ሆነ ለመወደድ ያለ ሰው ለብቻ ተነጥሎ ‹‹አንድ እንጨት ብቻውን አይነድም›› እንዲሉ ፍቅርን ለብቻ ማቀጣጠል የማይቻለው፡፡ እናነተ አይደለም ለፍቅር ለፀብም እኮ ሰው ብቻውን ይጣላው ከሌለው ከግንድ አይጣላ፡፡ ያለ ሰው ሰው መሆን ቢቻልም ሙሉ ሰው መሆን ግን አይቻልም፡፡ ምንም እንኳን በጉጥና በቀበሌ ብንከለል፣ ምንም እንኳን በሀይማኖትና በብሄር ብንለያይ አንድ ነገር ማወቃችን ግድ ነው ማንም ከደም ስሩ ደም ቀድቶ አስመርምሮ ደምክ የዚህና የዛ ብሔር ነው ብሎ ሀኪም ማረጋገጫ የሰጠው የለም፡፡ ደሞም ማንም ብሄልና ቋንቋው ቢለያይ ዋነው ነገር ሰው መሆንን ነውና ቅድሚያ ለሰው ሊሰጥ ግድ ነው፡፡

የዚህች ሀገር የትናንት ተሞክሮዋ ይሄው ነው፡፡ ማንም ማንንም በጥላቻ ተሞልቶ ወግድልኝ ከመንደር ሀገሬ ከማለት ይልቅ አይደለም ሰፈሩና ሀገሩ ዘልቆ ቤቱ የመጣን እንግዳ እግር አጥቦ፤ ቤት ካፈራው ምርጡን አብልቶና አጠጥቶ፤ ከመኝታው የከበረውን ስፍራ ለቆና ቢያጣ ቢያጣ እሱ ሳይበላ አብልቶ እሱ እየበረደው እንግዳውን ደርቦ አሙቆ ያስድራል የሀገሬ ደጉ ሰው ያለ ሰው መኖር ሞቱ የሆነው የፍቅር አርበኛው ያኢትዮጲያዊው ወገኔ፡፡

በአራቱም አቅጣጫ ካለው ወገኔ ጋር ከሚለየን ነገር ይልቅ አንድ የሚያደርገን ነገር ስለሚበዛ ሀይማኖትና በሔር ሳይገድበን አብረን ለዘመናት ኖረናል፣ አብረን ክፉ ደጉን አይተናል፣ አብረን ስቀን አብረን አልቅሰናል፣ አብረን ወድቀን አብረን ተነስተናል፡፡ ይህ ወገኔ እኔነቴ በሱ መልክ ውስጥ አለ ደሞም የኔ መልክ በሱ ውስጥ በሙላት ይታያል እናም ሁለታችንም የአንድ ወንዝ ጠጪዎች ኢትዮጲያ የምትባል የደጎች እናት የሆነች ሀገር ልጆች ነን፡፡

ጥላቻን ዘርቶ ፍቅርን ማጨድ ማሰብ በሰማይ ጤፍ ወቅቶ እብቁ አይኔ ገባ የማለት ያክል ነው፡፡ ፍቅርን አጨልሞ ለጥላቻ በር መክፈት በራሱ ከነፍስ ማጥፋት ወንጀል ጋር ተለይቶ አይታይም፡፡ ለዚህ ነው በየቅያችን ደግ ደጉን እያወራን ዛሬ የከበበንን ክፋት እንደ ልብስ አውልቀን በመጣል ከልዩነታችን ይልቅ አብሮነታችንን እናጠንክር መባሉ፡፡ ወገኖቼ እኛ ያለ ሰው ምንም ነን ምክኒያቱም በርካታዎቹ ብሮቻችን አፈር አያለብሱንም ስለዚህ ያለ ሰው ምንም ማድረግ አይቻለንም ተሳክቶልን ብንችል እንኳን እንደገና ነገራችን ሙሉ አይሆንም ምክኒያቱም ያለ ሰው ሰው ብቻውን ሙላቱ ምንም ነውና ነው፡፡

ዛሬ በዚህ ላብቃ፡፡ ደግነትን እናብዛ፣ ክፋትን እንቀንስ፣ ዛሬ የምንበላው ካለን ከቻልን እናካፍል እንጂ አንንጠቅ፣ የሌሎችን ፍቅርና ይሁንታ ለማግኘት ከልዩነታችን የሚበልጠውን አንድነታችንን ዋጋ ሰጥተነው እንከባከበው፡፡ ሰው ያለ ሰው ምንም ነው ነውና ሰው ከሆንን ሰዎችን አናግልል፡፡ ከሰው ጋር........ቸር ሁኑልኝ፡፡

## የልዑል . . .

ከገጽ 5 የዞረ

በአንድ ወር ውስጥ ወደ 92 ሺህ ከፍ ብሏል፤ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ተመልካቾችንም ማግኘት ችሏል።

በርግጥ ስድስት ዓመታት የለፋበትን ስራ፣ ብዙ ገንዘብ የወጣበትን አልበም ገና ያድጋል ተብሎ በሚጠበቅ ቻናል መጫን ድፍረትን ይጠይቃል። ልዑል ደፈረ፤ ተሳካለት፤ ብዙ ተመልካቾችን ማግኘት ችሏል። ለነገ የሚሆን ፕሮጀክትም በመፍጠር ሂደት ውስጥ አልፏል። በዓለም አቀፍ ደረጃም ዝነኞች ስራዎቻቸውን በራሳቸው ዩቱዩብ መጫንን ቴክኖሎጂን ከማማረር ወደ ማመስገን እንዲያመዝኑ አድርጓቸዋል።

ደግሞስ ታዋቂ ዩቱዩብ ቻናል የዘፋኙን ስራ በርካሽ ገዝቶ እስከ 20 ሚሊየን ተመልካች ሲያገኝበት ሚሊየን ብርን ሲሰራበት ፣ ዘፋኙ ግን 3 መቶ ሺህ ብር ይዞ (ለዚያውም ዝነኛ ከሆነ ነው) ሲቀር እስከ መቼ? ቀድሞ ሙዚቃ ቤቶች አንድ ካሴት በ3 ሺህ ብር ገዝተው እስከ 3 መቶ ሺህ ብር ድረስ እያባዙ ይሸጡት ነበር። ዘፈኑ የፈለገውን ያህል ቢወደድም፣ ቢሰራጭም ፣ሚሊየን ብርም ቢሸጥ ዘፋኙ ያው 3 ሺህ ብሩን ይዞ ይቀራል።

ሙዚቃ ቤቱ በዘፋኙ ስራ ይበለጽጋል። ዘፋኙ በድህነት ውስጥ ይቀጥላል። ድጋሚ ካሴት ለመስራት አቅሙ ይሰለባል። ዘንድሮም በሚሊየን ተከታይ ያላቸው ዩቱዩብ ቻናሎች የድሮውን መንገድ ተከትለው ሙዚቀኛውን እየበደሉት ነው። እነሱ በሚሊዮን፣ ዘፋኙ በመቶዎች ይጫዎታሉ። የልዑል በራስ ቻናል መምጣት ይህንን በደል መከላከል ምርጥ መፍትሔ ነው።

## በድሬዳዋ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

አስተዳደሩ ማመንጨት የሚገባውን ያህል ገቢ ለመሰብሰብ ታዲያ ባለስልጣኑ በቴክኖሎጂ የታገዘ አዲስ አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ገልፀው፤ በተሰራው ስራም ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገር መቻሉን አስታውቀዋል።

በተከናወነው ስራም በግማሽ በጀት ዓመት ቀጥታና ቀጥታ ካልሆኑ የገቢ ርዕሶችና ከማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ከ2 ቢሊዮን 335 ሚሊዮን ብር በላይ በመሰብሰብ የተሻለ ስኬት ተመዝግቧል ብለዋል። ገቢው የዕቅዱን 87 በመቶ ማሳካት የቻለ ሲሆን ከአምናው ተመሣሣይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ295 ሚሊዮን ብር ብልጫ ማሳየቱን ነው የገለፁት።

በተከታታይ ዓመታት በተሰሩ ስራዎች በግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ዘንድ ግብርን በወቅቱ ለመክፈል እየተፈጠረ የሚገኘው የአስተሳሰብ ለውጥ ለዚህ ስኬት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ተናግረዋል። የአስተዳደሩ ከንቲባና ከፍተኛ አመራር አባላቱም ለባለስልጣኑ እያደረጉ የሚገኙት ድጋፍ፣ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ያህል ገቢ ለመሰብሰብ የሚደረገውን ጥረት ውጤታማ አድርገውታል ብለዋል።

ባለፈው ዓመት 3 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን አስታውሰው፤ በዘንድሮው አመት 5 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የአስተዳደሩን ወጪ በራሱ ገቢ ለመሸፈን እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል። መረጃው የኢዜአ ነው፡፡

## ወልደ . . .

ከገጽ 8 የዞረ

ህይወት በፍጥረት ምርመራ ርዕስ የሰውን ልጅ ነፍስ ዘላለማዊነት መሰረት አስይዞ ይጠናቀቃል፡፡

እንግዲህ በወልደ ህይወት ምርመራ እንዲህ ከፍ ያለ ማዕረግና ስፍራ ያገኘችው የሰው ነፍስ የዕውቀት ሁሉ መውጫ መሆኗን በእሱው ሐሳብ ከጨበጥን በዚህች ነፍስ ሊመረመር የሚገባውስ እውነት ምን ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም፡፡ እንደ እሱ አስተሳሰብ ፈጣሪ እውነትን እናውቅባት ዘንድ በፈጠረልን ነፍስ አስቀድመን ልናውቅ የሚገባን “ እምነትን” ነው ይለናል፡፡ ይህን የአስተሳሰብ ታላቅ መገለጫና አያሌ የእምነት ሰዎችን በየትውልዱ ሲያስቆጣ የቆየውን “የእምነት መመራመር” ጉዳይ በቀጣይ ሳምንትስንገናኝ እንቀጥላለን ፡፡ ቸር ሰንብቱልኝ፡፡

አመሰግናለሁ

ማጣቀሻ ፦ ጥበብ ከጺላጦስ ቁ.2

# የልዑል አዲስ ስራ

ሙዚቃ በየዘመናቱ በቴክኖሎጂ እየተፈተነም ሊገታ ያልቻለ ድንቅ ጥበብ ነው። የቀድሞዎቹ አንጋፋ ድምጻዊያን በኢኮኖሚ ተጎድተውበት ዝና እና የሙያ ፍቅርን አስቀድመው የዛሬውን የሙዚቃ መልክ ሰርተውት አልፈዋል። ጥቂት የተሳካላቸው የቅርብ ጊዜ ወጣትና አንጋፋ ድምጻዊያን ዛሬም በዘርፉ ውስጥ ተስፋ አላቸው። አሁን የቀድሞዎቹ የሙዚቃ ስራ መስመሮች ተዛብተዋል፤ ሥርዓቱ ተለውጧል።

ሙዚቃ አሁን ዩቱዩብ የሚባል ቴክኖሎጂ ላይ ወድቋል። ኢንተርኔት ባለበት ብቻ ገንዘብ ይሰራል። ግጥምና ዜማ ሰብስቦ ከሙዚቃ ቤት ጋር ተነጋግሮ ካሴት ማውጣት ቀረ። ካሴቱን ሸጦ ገንዘብ ማግኘትን ዘመን ጣለው። አሁን አልበም መስራት ከ6 እስከ 8 ዓመታትን ሲወስድ በብዙዎች ድምጻዊያን አይተናል። ሙዚቃ አልሰራም ብለው ቴክኖሎጂው ገፍቷቸው ከዳር የቆሙም አሉ። ቀደም ብሎ በ1970ዎቹ ሙዚቃ በየዓመቱ የሚያስደምጡን ነበሩ።

ያን ጊዜ በትንሽም ብር ቢሆን ካሴታቸውን የሚገዛቸው ሙዚቃ ቤት ነበር። ቢያንስ አይከስሩም። ዛሬ ግን ካሴት ተሰርቶ የት ይሸጣል? ማንስ ይገዛል? ወጪውንስ ማን ይችለዋል? ለዚህ ነው ብዙው ዘፋኝ እንደምንም ተጣጥሮ አንዷት ነጠላ ዜማ ይለቅና ኮንሰርትም ምንም ሰርቶ ለመኖር ጥረት ሲያደርግ የምናስተውለው።

አልበም መስራት ዘንድሮ ራስ ምታቱ ከባድ ነው። ሙዚቃ ቴክኖሎጂው ጋር ትብብር የፈጠሩና የገንዘብ አቅም ያላቸው ብቻ የሚጫወቱበት ጥበብ ሆኗል። ርግጥ በርካታ ወጣቶች የኢኮኖሚ ጫናውን ተቋቁመው፣ ወጪውን ሁሉ ችለው ነጠላ ዜማዎችን እየሰሩ ናቸው። ዘርፉ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ እንጂ መልሶ የማይከፍል በመሆኑ ወደ ፊት ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ብቻ የሚሰሩበት እንዳይሆን ያስፈራል።

ሙዚቃ ወረደ፣ ዜማው፣ ግጥሙ፣ ቅንብሩ፣ ቪዲዮው በትክክል አልተሰራም ብሎ ለመናገርስ በነጻ ከኢንተርኔት አውርዶ የሚያደምጥ ሰው ምን ሞራል አለው? የማይከፍል ጥበብ ጉዞው እስከምን ድረስ ነው? በርግጥም የወጣቶችን ድምጻዊያን ዘፈኖች ተቀብለው የሚያሰራጩ፣ ዝግጅቱን በገንዘብ ሸፍነው የሚያሰሩ፣ የተጠናቀቁ ዘፈኖችን በገንዘብ ተምነው የሚገዙ የዩቱዩብ ቻናሎች አልታጡም።

አንዳንዶቹ ድምጻዊያን በልመና ስራዎቻቸውን ግዙን ብለው ለምነው ዩቱዩቦች ከተቀበሏቸው በኋላ ገንዘብ እንዳልሰጧቸውም ነግረውኛል። ስምና ዝና የሌላቸው ጀማሪዎች ተኮላሽተው ከሙዚቃ ሙያ ተገፍተዋል። ይህ ሁሉ ችግር እያለ፣ ሙዚቃ ኢትዮጵያ ውስጥ በገንዘብ ተሰርቶ በነጻ ለሕዝብ ሊታደል አልበም ይሰራል። አሁንም የግጥም ዜማና የሌሎችን ወጪዎች ለመሸፈን የሚቻለው በዩቱዩብ ከኢትዮጵያ ውጪ ሙዚቃዎች ሲታዩ በሚተላለፍ የማስታወቂያ ገቢ ነው። ሙዚቃ ከሚጭኑ ቻናሎች ይልቅ በራስ ዩቱዩብ ቻናል መምጣትን ወጣቶች ምርጫ አድርገውታል።

በርግጥም ቻናሉን ማሳደግና ምርጥ ስራዎችን ይዞ መምጣት ከኪሳራ የሚታደግ ስልት ነው። ቴዲ አፍሮ ባለው ስምና ዝና የአልበም ሲዲውንም ሸጧል፤ በራሱ ዩቱዩብም በመጫን ከጥበብ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም አግኝቷል። ሁለቱን ቴዎድሮሶች መሆን ነበር የምፈልገው የሚለው ልዑል ሲሳይ የቴዲ አፍሮን መንገድ ተከትሎ መጥቷል።

ከሰሞኑ ልዑል በሚል መጠሪያ ለህዝብ በነጻ ያደረሰው አልበሙ በስፋት እየተደመጠለት ነው። ጉዞውን እንመልከተው እስኪ፤ የልዑል ሙዚቃ ሕይወት ብዙ ውጣ ውረድ የታለፈበት ነውና ካለፉት የሙያው ሰዎች የወሰደው ትምህርት አለ። ዘመኑ የፈጠረውን የቴክኖሎጂ እድል እና ፈተና በመረዳት በጥበብ መጠቀም የሚችልበትን መስመር የተከተለ ይመስላል።

ቴዎድሮስ ታደሰን እና ቴዎድሮስ ካሳሁንን በዘፈን አቅማቸው ሲያደንቅ ያደገው ወጣቱ ድምጻዊ ልዑል በልጅነቱ ወታደር የመሆን ፍላጎት ነበረው። በአሥራ አንድ ዓመቱ በሜሪ ጆይ ድርጅት አማካይነት ሙዚቃን እንዲያቀርብ ዕድሉ ተፈጠረለት። ለመጀመሪያ ጊዜ ጓደኞቹ ፊት በኪቦርድ ታጅቦ ዘፈን አቀረበ። በተስፋዬ አበበ ኪነጥበባት ድርጅት ውስጥ ቴያትርና ሙዚቃ አጥንቷል። በኮካ ኮላ ሱፐር ስታር የድምጽ ውድድርን በ17 ዓመቱ በ2ኛነት አሸንፏል።




በመቀጠል ኤክስፐረስ ባንድን ተቀላቀለ። ልዑል በሙዚቃው ልምድና ዕውቀቱ እያደገ ሲመጣ ራሱን የበለጠ ወደ ሕዝብ ማድረስን ማሰብ ጀመረ።ተስፋዬ አበበ ግጥምና ዜማ እንዲሰሩለት ጠየቃቸው። ኂሩት በቀለ እና ታደለ በቀለ አይነ በጎ በሚል ያቀረቡትን ዘፈን ግጥም ዜማ የሰሩት ተስፋዬ አበበ ናቸው። ለምን ይህንን ከእቴነሽ ደመቀ ጋር አትዘፍኑትም ሲሉ ለብላቴናው ልዑል ሐሳብ አቀረቡለት። እንዳሉትም ልዑል ይህንን ዘፈን በደስታ በኤክስፐረስ ባንድ ታጅቦ አቀረበው። ልዑል የሚባል ለጋ ወጣት በጥሩ ድምጽ የሙዚቃውን ዘርፍ ተቀላቀለ።

ቀረሁ እንጂ ሲልም ሌላ አንድ ዘፈን ከኤክስፐረስ ባንድ ጋር በማቅረብ ከሕዝብ ጋር ትውውቁን አጠናከረ። ሰላም ትሙት በሚልም ሀገራዊ መልእክት ያለው ሌላ ዘፈንን አቀረበ። ያለፉትን ስድስት ዓመታት አልበም በማሰናዳት ላይ ከርሞ "ልዑል" ያለውን አልበሙን 14 ዘፈኖችን በማካተት ለአድማጭ አድርሷል። "የድምጻዊነቴ ምስጢር እናቴ ነች" የሚለው ልዑል እናቱ ሙዚቃን የምትወድና ነዋይ ደበበን በልዩነት የምታደንቅ ስለመሆኗ ይናገራል።

ይህ የእናቱ ተጽእኖ አድሮበትም ይመስላል ልዑል ለመጀመሪያ ጊዜ መዝፈን ሲጀምር የነዋይ ደበበን ማዕበል ነው የሚለውን ዘፈን የዘፈነው። እናቱ እንደ ቀደሙት ወላጆች አዝማሪ አትሆንም ብላ አልተቆጣችውም፤ ልጇ ምኞትና ፍላጎቱን እንዲያሳካ፣ በሙዚቃ ልምምድ ወቅት እንዳይቀር በዘፈኑ እንዲገፋበት ደገፈችው እንጂ። ልዑል አልበምን ከመስራቱ በፊት አልበሙ ተሸጦ ገንዘብ እንደማያስገኝለት፣ ቴክኖሎጂው ከቁጥጥር ውጪ መሆኑን ተረድቷል። ለዚህም በስሙ ዩቱዩብ ከፍቶ ሌሎች ዘፈኖችን በመጫን እያሳደገና እያስተዋወቀ ተጉዟል።

ኢትዮጵያን በሚመለከት በተመሳሳይ ቅኝት የተሰሩ የሌሎች አንጋፋ ድምጻዊያን ስራዎችን በአንድ ስብስብ በማቅረብ ቻናሉን አሳድጓል። የሙዚቃ አቅሙንም አጎልብቷል። የቴዎድሮስ ታደሰ፣ ፀሐዬ ዮሐንስ፣ ነዋይ ደበበ፣ አስቴር አወቀ፣ ብዙአየሁ ደምሴ፣ እጅጋየሁ ሽባባው፣ ብርሀኑ ተዘራ እና ቴዲ አፍሮ ዘፈኖችን አካቷል። ቴዎድሮስ ታደሰን በማድነቁ የእሱን ዓይነት አልበም መስራት ፍላጎት አድሮበታል። ከሙዚቃ አቀናባሪው ኪሩቤል ተስፋዬ ጋር የቴዎድሮስ ታደሰን የመሰለ አልበም ነው መስራት የምፈልገው ብሎ መከረ። ልዑል ለቴዲ አፍሮ ልዩ አድናቆትና ክብር እንዳለው ይናገራል።

ልዑል በሚሰራበት ቦታ አንድ ቀን ቴዲ አፍሮ ድንገት በእንግድነት ተገኘ። "በርታ ጥሩ አቅም አለህ" የሚል ሙገሳ ከቴዲ አፍሮ ቀረበለት። ይህ አድናቆት ሌላ ጉልበት እንደሰጠው ልዑል ያስታውሳል። በሌላ ቀን ቴዲ አፍሮ ልዑልን አግኝቶ መከረው፤ የህይወት ልምዱን አጋራው።

በርታ ሲልም "መልኬ በቃኝ" የተሰኘውን ዘፈን ግጥምና ዜማ በስጦታ አበረከተለት። ልዑል አልበም ስኬታማ እንዲሆን ቴዲ አፍሮ የሙያ እና የሐሳብ ድጋፍ እንዳደረገለት ወጣቱ ድምጻዊ ተናግሯል። ልዑል አልበም 14 ዘፈኖችን አካቷል። ሁለቱ በትግርኛ ቋንቋ ቀርበዋል። ሞገስ ተካ፣ እሱባለው ይታየው፣ ደጎል መኮንን፣ ቴዲ አፍሮ፣ምሕረት አብ ደስታ ፣ ወንድወሰን ይሁብ በግጥምና ዜማ ስራዎች ተሳትፈውበታል። ኪሩቤል ተስፋዬ 13 ዘፈኖችን ማስተሪንግ፣ 12ቱን ቅንብር ሰርቷል። ብዙዎችን ዘፈኖች ደግሞ በቤዝጊታር አጅቧል። አቤል ጳውሎስ ደግሞ መልኬ በቃኝ የሚለውን ዘፈን አቀናብሯል። ኤክስፐረስ ባንድ ውል አለችን ሲያጅብ ፈለቀ ኃይሉ ቅንብሩን ሰርቷል።



መዋብም ማጌጥም ለራስ ነው

መልኬ ብቻ በቃኝ ብሎ ኩራት ምንድን ነው

ምን ቢይምር ቁንጅና ቢደነቅ

አለ አመል አይደምቅ

እንዲህ አሳምሮ በሰራሽ ፈጣሪ

ተውቤያለሁ ብለሽ በመልክሽ አትኩሪ

እንኳንስ ቁንጅና የሚመኩበት

ማን አለወይ ብሎ ይቀራል ከሞት

እኔን አይመስለኝም መልክ ብቻ ቆንጆ

አመል ከሌለበት ያፈርስ የል ወይ ጎጆ

የቴዲ አፍሮ ግጥምና ዜማ ነው ይህ የልዑል ዘፈን። አካላዊ ውበት በተፈጥሮ የሚቸሩት ነው። ቢንከባከቡት እንጂ የሰው ልጆች አይፈጥሩትም። ውበት ብቻውን እንደ ጽጌረዳ አበባ ሲያዩት የሚስብ ግን ደግሞ እንደ እሾህ የሚዋጋ ነገር ነው።ውበትና ጸባይ ካልተስማሙ ሁሉም ከንቱ ይሆናሉ።ውበትሽ እንደሚረግፍ አትዘንጊ ይላል ዘፋኙ። ልቤ በውበትሽ ተማርኮ ቢወድሽም፣እንኳን ከሰው ማደሪያው አመል ከሌለሽ ሁሉ ከንቱ ሆነብሽ ይላል። ልቤ ካንቺ ጋር የሚቆየው በውበትሽ አይደለም፤ እባክሽ በጊዜ በዘመን የማይለወጠውን የፍቅር መሰረት የሆነውን ባህሪሽን አስተካክይ፤ አጉል ኩራት ይቅርብሽ ብሎ ይመክራል።

ባያት የሚለው ሌላው የልዑል ዘፈን በመልዕክቱ ለየት ብሎብኛል።የሰው ልጆች ሁሉ የታደሏትን አንድ የጋራ ሀብት ያነሳሳታል። በአፈጣጠሯ፣ በዘመድ እና ወላጅ አልባነቷ ይገረማል።አንድ ፈጣሪ አላት። ከማንም ተፈጥራ ግን ደግሞ ራሷን ለሁሉም እኩል የሰጠች ረቂቅ መንፈስ ናት። ዘር የሌላት የብዙዎች ማደሪያና የአንድነት ካስማ ናት። ቢያያት፣ ቢመለከታት እናቴ ትሙት፣ አባቴ ይሙት አትልም። እናትም አባትም የሌላት ለሰው ልጅ የምትኖር ራሷ ግን ብቸኛ ናት።

ካህንና ንጉሥ ሆና የራስ ወርቅ ዘር መዛ ስትቀጥፍ ካንገት በላይ ሳቅ እንደ ውሸት ቀላ ረክሳ እንዳትሞት ያለ ዘር ፈጠራት ፍቅርን ያለአባት ያለ ዘር ፈጠራት ፍቅርን ያለ እናት ዘንድሮ እንደ ሀገር የምንጣላበት ምክንያት መፍጠሩ እየቀለለን ነው። በተፈጥሮ ሀብት፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በአካባቢ፣ በሐሳብ፣ በጥቅም እና በሌሎችም የሰው ልጆች ግጭት ውስጥ ይገባሉ። እኔ ልቅደም፤ እኔ እበልጣለሁ፤ ለእኔ የተሻለ ነገር ይገባኛል፤ የእኔ ነው በሚል ነው ግጭቶች የሚባባሱት። ልዑል አምላክ የፈጠራትን ረቂቅ ስሜት ሁሉም እንዳይጣሉባት ዘር እና ባለቤት አልባ አድርጓታል ይላል። ይህችን ስሜት አምላክ በአፈጣጠር ጥበቡ እንደታደጋት ዘፈኑ ይገልጻል።

መስጥሮ ባይፈጥራት ቃል በልታ ባትጸድቅ ስትሾመን ስንቀጥፋት ከስማ ብትቀር ዘር መዞ ቢፈጥራት እንደሰው ፍቅር ህይወት ከዚህ ከፍታ ምን ልትሆን ነበር ከዚህ በላይ ከፍታ ሰርክ ያለም ጀንበር ምን ልትሆን ምን ልንሆን ምን ልንሆን ነበር ፈጣሪ ፍቅርን ያለ ዘር ስለፈጠራት ከጥል እና ግጭት ምክንያትነት አድኗታል። እንደ ብሔር፣ እንደ ቋንቋ፣ እንደ ሀብት፣ እንደ ሐሳብ የኔ ነው በማለት የሰው ልጆች አልተጣሉባትም።

እንዲያ ባይሆን ምን ይውጠን ነበር ሲል በፍርሀት ያንጎራጉራል። ፍቅር ዘርና ባለቤት የለሽ ረቂቅ ስሜት ናት። የኔ አመል ከተወደዱት የወጣቱ ድምጻዊ ልዑል ሲሳይ ዘፈኖች መካከል አንዱ ነው። ከመፈቀር ማፍቀር ጥሩ ነው የሚሉ ሰዎች አሉ። በማፍቀር ውስጥ ርግጠኝነት አለ የሚል ነው የሰዎች እሳቤ። የኔ አመል አንድ ነው፤ በጊዜ በሁኔታ የማልለወጥ ታማኝ አፍቃሪ ነኝ፤ ሰዎች ሲለወጡ አይቻለሁ፤ ርግጠኛነትን ካንቺ እፈልጋለሁ ይላል በዘፈኑ።

አንቺም ካንደበትሽ የሚወጣውን

አምኜ እንድቀበል የምሰማውን የምትይው ሁሉ እውነት ለመሆኑ

ርቀን ሳንሄድ ንገሪኝ ካሁኑ

ሰበብ ላታበዢብኝ ምክንያት ላትደረድሪ

ግማሽ አካሌ ሆነሽ ከኔ ጋራ ልትኖሪ

ቃልሽ የማይለወጥ ከሆነ ነው በይኛ

እስኪ በፈጣሪ ስም ምለሽ አረጋጊኛ

ቀርበሽ እንደማትርቂኝ

እንደምታዛልቂኝ

ሳምንሽ እንደማትከጂኝ

መቼም እንደማትጎጂኝ

ዐይን ዐይኔን እያየሽ ንገሪኛ

በይ አውሪኛ

እኔም ተማምኜ እንድቀርብሽ አድርጊኛ

ይህ አፍቃሪ ወይ ከቀደመ የፍቅር ሕይወቱ አሊያም ደግሞ ከሰዎች በማየት ጥርጣሬ አድሮበታል፤ የፍቅር ሕይወት ለመጀመር ይፈራል። የያዝሁትን ልብ እንዳታስጥይኝ፣ ልቤ ስስ ናት፣ ትተሽኝ እንደማትሄጂ ርግጠኛ ካልሆንሽልኝ የጀመርነውን ግንኙነት እናቋርጥ የሚል ይመስላል። እስኪ በፈጣሪ ማይልኝ የሚለው ያለ አንዳች ነገር አይደለም፤ የቀደመ መከዳት የደረሰበት አፍቃሪ ሳይሆን አይቀርም።

አብራው እያለች ፍቅር እየሰጠችው እሱ የሚፈራው "ግን የምርሽን ነው?" እያለ ትታኝ ትሄዳለች ብሎ ይፈራል። መጎዳት ያንገሸገሸው አፍቃሪ በመሆኑ ዐይን ዐይኔን እያየሽ ንገሪኝ ሲል ይለምናታል። እውነትና ውሸትን ከዐይኗ ለመለየት።የቀደመ የፍቅር ሕይወት ጠባሳ በሙሉ ልቡ እንዳይቀርባት እንቅፋት ሲሆንበት በእንስፍስፍ አንጀቱ እንዳትመጣበት አመሌ አንድ ነው እባክሽ ሲል እናደምጣለን። ልዑል ሲሳይ በራሱ ዩቱዩብ ቻናል መምጣቱ ዘርፉ አሁን ያለበትን ችግር በውል የተገነዘበ መሆኑን ያሳያል። በአሁኑ ጊዜ ከማህበራዊ ሚዲያ ገንዘብ በመክፈል ዩቱዩብ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ልዑል ዩቱዩቡን ለማሳደግ የሌሎችን ዘፋኞች ስራዎች በማቅረብ ሲሰራ ቆይቷል።

አልበም መዳረሻ፣ የመልካሙ ተበጀ በእንባ ተለያየን፣ የቴዎድሮስ ታደሰ እቴ በገላሽ፣ የጥላሁን ገሰሰን ከረምኳታ ዘፈኖችን እንደገና በመጫዎት ሚዲያውን አስተዋውቋል። በራሱ አልበም ሲመጣ ደግሞ ከ25ሺህ ገደማ ተከታይ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አረንጓዴ ልማት

በበድሉ ሀይሌ



በዓለማችን በየጊዜው የሚከሰተው የአየር ንብረት ለውጥ ስጋት መሆን ከጀመረ በርካታ ጊዜያትን አስቆጥሯል። ለውጡ በዓለም ላይ እየደረሱ ላሉ ተግዳሮቶችና ለአዞን መሳሳት መንስኤ ሆኖም ይታያል። ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሱት ደግሞ ወደከባቢ አየር የሚለቀቁ የበካይ ጋዞች ልቀት መጨመርና የደን ሀብት እየተመናመነ መምጣት ነው።

በአየር ንብረት ሚዛን መዛባት ምክንያት የበረዶ ግግር እየቀለጠ፣ አካባቢን ለውሃ መጥለቅለቅ አደጋ እያጋለጠ፣ በአውሎ ንፋስና በእሳት አደጋ የሰው ህይወትና ንብረት እየጠፋ ነው፡፡

መሬት እየተደረመሰና ህንፃዎች እየፈራረሱ፣ የፀሐይ ንዳዱም ህይወት ያለውን ፍጡር እስትንፋስ እያሳጠረ ስለመሆኑ ዓለማችን ያስተናገደቻቸው ክስተቶች ይመሰክራሉ፡፡ የአለም መሪዎች በኳታር በተካሄደው የዶሃ ጉባዔ ስምምነት ላይ ምንም እንኳን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ ልቀት መጠንን ለመቆጣጠር ስምምነት ላይ ቢደርሱም፤ የምድር ሙቀት ከዕለት ወደ እለት እየጨመረ መምጣቱን ቀጥሏል። በዚህ የተነሳ ምድራችን በቅርቡ መቋቋም የማትችለው ሙቀት እንደምታስተናግድ፤ የምድር የውሃ አካላትም ከፍታቸው እንደሚጨምር ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

የሰውን ልጅ በከፍተኛ ሁኔታ እያሳሰቡ ያሉት የአየር ንብረት ለውጥና ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች አጠቃላይ የምድርን ተፈጥሯዊ ሂደት እየጎዱት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ከምድራችን ጋር ያለንን ግንኙነት ካስተካከልን የወደፊቱን እጣ ፈንታ ማስተካከል እንችላለን፤ ካልሆነ ደግሞ ለከፋ ችግር ይዳርገናል ማለት እንደሆነ ጥናቶቹ ያሳያሉ። በጥናቶቱ እንደ መፍትሄ ተብለው የተቀመጡት ደግሞ ለተለያዩ ግልጋሎቶች ብለን የምናቃጥላቸውን ነገሮች መቀነስ፤ ብዙ ዛፎችን መትከል፤ ጥቅጥቅ ደኖቻችንን መንከባበከብና ካርቦንዳይ አክሳይድን ከከባቢ አየር መምጠጥ የሚችሉ የፈጠራ ውጤቶችን ማበረታታት ይጠቀሱበታል።

አጼ ኃይለ ሥላሴ ደን መጠበቅና ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ፓርኮች እንዲቋቋሙ ምክንያት ሆነዋል። ለዚህም አዋሽ ብሔራዊ ፓርክን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። በደርግ ዘመነ መንግሥትም የአካባቢ ጥበቃን የተመለከቱ ፖሊሲዎች ተቀርፀዋል። ዋነኛ ትኩረታቸው ግን የዱር እንስሳት ጥበቃ ላይ እንደነበር ጥናቶች ያትታሉ። በተለይ በጎርጎሳውያኑ አቆጣጠር 1973/74 (1966 ዓ.ም) በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የተከሰተው ርሃብና ድርቅ፤ አካባቢ ጥበቃ ላይ ጠንክሮ ለመስራት ካነሳሱት ጉዳዮች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

በአጠቃላይ ደን ሥራ ላይ ከፍተኛና የተቀናጀ ስራ ለመስራት ዝግጅት ተደርጎ፣ ቦታዎች ተመርጠው፣ ችግኞች ተፈልተው፣ ለማህበረሰቡ አነስተኛ ድጎማ በማድረግ፤ በተራቆቱ ቦታዎች ችግኞች እንዲተከሉ በርካታ ሥራዎች መሰራታቸውን ሰነዶች ያረጋግጣሉ። በተራሮች ላይ በብዛት የሚታዩት ደኖችም በዚያ ዘመን የተተከሉ ናቸው ይላሉ። ጥናቶች እንደሚያሳዩት የችግኝ መትከል ዘመቻዎችን ለማካሄድም በዋነኛነት ለሰዎች ማበረታቻዎችን በመስጠት፤ ለምሳሌ እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ቦታዎች የእርዳታ እህል ለመስጠት ችግኝ እንዲተከሉ ይደረግ ነበር።

“ለትምህርት ቤት ደብተር መግዣ ችግኝ ተክለን ገንዘብ ይከፈለን ነበር” ሲሉ የራሳቸውን ተሞክሮ የሚያቀርቡ ሰዎችም አሉ። በቀድሞ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ ጊዜ በተለይ ዋናው የትኩረት አቅጣጫ የአየር ንብረት ለውጥ በመሆኑ ችግኝ መትከልና አካባቢን መንከባከብ እንደ አንድ ትልቅ ሥራ እንዲወሰድ በርካታ ሥራዎች ይከናወኑ ነበር። ይህ ወቅት የልማትና የአካባቢ ጥበቃ ተቋማት የተመሠረቱበትም ነው። በፖሊሲ ደረጃም ሥነ ምህዳርን፣ አካባቢን፣ የተፈጥሮ ሐብት ጥበቃን በሚመለከት ግብ ተቀምጦለት እንቅስቃሴ የተጀመረበት ነው።

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን እየመሩ ያሉት ዶክተር ዐብይ አሕመድም ‘አረንጓዴ አሻራ’ በሚል አገር አቀፍ የችግኝ መትከል ዘመቻ በተከታታይ አካሂደዋል። ዘመቻው በፍላጎት ላይ የተመሠረተ እና በስፋት በርካታ ችግኞች መተከላቸው ቀደም ካሉ ዘመናት ልዩ ያደርገዋል፡፡ እንደ ኢትዮጲያ ላለ ታዳጊ ኢኮኖሚ እድገት ያላቸው ሀገራት የተፈጥሮ ሀብቶች ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ግዴታ የሚሆንባቸው እድሎች ሰፊ መሆኑን የሀገራት ልምድና ነባራዊ እውነታ ያሳያል፡፡

ኢትዮጵያም ካሏት እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶችና የመልሚያ እድሎች አንዱ የደን ሀብት ሲሆን የደን ሀብቶችን መጠበቅ፣ ማልማት እና በዕቅድ ጥቅም ላይ ማዋል ኢኮኖሚያዊ፣ ሥርዐተ-ምህዳራዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን እልፍ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ እንደ ሚያመለክተው በኢትዮጵያ 83 በመቶ ህዝብ ነዋሪነቱ በገጠር እንደሆነ ነው። ይህ ማለት በርካታው የአገራችን ህዝብ አኗኗር በአንድም ሆነ በሌላ ከግብርና ጋር የተሳሰረ እንደሆነ መገመት አያዳግትም። በመሆኑም በዚህ መሰረተ ሰፊ በሆነው ዘርፍ ላይ የሚደረግ ርብርብ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ ለውጥ ለማምጣት የማገዝ ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም ሀገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥ በግብርና ምርታማነት ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ቀድማ በመገንዘብ የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን እየተከተለች ትገኛለች። የኢትዮጵያ ፈጣን ዕድገትና የአረንጓዴ ልማት ስራዎቻችን ተመጋጋቢነት ናቸው። የአካባቢን ጥበቃ መሰረት ያላደረገ ፕሮግራም በየትኛውም መስፈርት ወጤታማ ሊሆን አይችልም።

የበርካታ አገራት በተለይ በተፈጥሮ ሃብት ላይ የተመሰረተ ዕድገት እያስመዘገቡ ያሉ አገራት የኢኮኖሚ ዕድገታቸው በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ብክነት በመፍጠር ላይ ነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆኑት ነዳጅ አምራች የሆኑ አገራት ለአካባቢ ብክለት ትልቅ ድርሻ መያዛቸው ነው፡፡

የሰው ልጅ በህይወቱ ወሳኝ የሆኑ ነገሮችን በአካባቢ ብክለትና ብክነት ያጣል። ይህም ደግሞ የሚከናወነው በዋናነት በሰው ልጅ ሲሆን ሌላው በተፈጥሮ መሆኑ ነገሩን አስገራሚ ያደርገዋል። ብክነት ሲባል የአካባቢ የሃብቶች፣ በተለይም የተፈጥሮ ሃብቶች በአግባቡ አለመያዝ ማለት ነው። ብክለት የአንድን አካባቢ (አፈር፣ ውሃ፣ አየር፣ ድምፅ...) ፊዚካላዊና ባዮሎጂካላዊ ይዘቶች ማጥፋት ወይም ማበላሸት ማለት ነው።

ብክለት የተፈጥሮን ወይም ሰው ሰራሽ ሀብቶችን በመበከል በሰው፣ በእንስሳትና በሌሎች ህይወታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ጉዳት ማድረስን ያጠቃልላል፡፡ የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው ጥረት ማድረግ እና ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ልማት አካባቢ ደህንነትን የሚያናጋ መሆን እንደሌለበት እንዲሁም ማንኛውም ሰው ጤናማና ንጽህ አካባቢ የመሮር መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገቷን በማረጋገጥ ድህነትን ለመቀነስና ዘላቂ ብልፅግናዋን ለማረጋገጥ የምታደርገው ጥረት በአብዛኛው የተፈጥሮ ሀብቶቿን በተገቢው መንገድ ከመያዝ፣ ከማስተዳደር እና ጥቅም ላይ ከማዋል ጋር የተያያዘ ነው። ከነዚህም ተፈጥሮአዊ እምቅ ሀብቶች ውስጥ የግብርና፤ ታዳሽ የኃይል አማራጮች ግንባታና አቅርቦትን ማሳደግ፤ ተደራሽ የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦትና የሠው ሀብት ልማትን ታሳቢ ያደረገ ዘላቂ ልማትን መሠረት ያደረገ ነው።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የጋዝ ልቀትን የመቀነስ፣ ከፀሀይ ኃይል ኤሌክትሪክ የሚያመነጭ ቴክኖሎጂዎችን በአማራጭነት የመጠቀም፣ የተፈጥሮ ሀብቷን በተገቢው የመገልገል፣ የተፋሰስ ልማትን የማስፋፋትና፣ የደን ልማትን በስፋት የማካሄድ ስትራቴጂዎችን በዋናነት በመቀበሏና ለተግባራዊነቱም ቁርጠኛ አቋም ያላት መሆኑን በአረንጓዴ ልማት ዙሪያ በነደፈቻውና መተግበር ላይ ባላቸው ስትራቴጂ አሳይታለች፡፡

የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂን በመጠቀም የአካባቢ ጥበቃ መሠረት ያደረገው ቴክኖሎጂዎች መካከል የተጎዱ መሬቶችን ከእንስሳትና ከሰው ንክኪ ነጻ በማድረግ እንዲያገግሙ የማድረግ አንዱ ነው። ይህም ቴክኖሎጂ በእፅዋት ሽፋን መሳሳትና በአፈር ለምነት መቀነስ ሣቢያ የተጎዱና ምርታማነታቸው የተቋረጡ መሬቶች መልሰው እንዲያገግሙ ከማድረግ አንፃር የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ቴክኖሎጂው የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ እንዲያገግሙ ለማድረግ በየአካባቢው መልክዓ ምድር ሊተገበር የሚችል ነው፤ ለአካባቢው አየር ፀባይ ተስማሚ የእጽዋት ዝርያ በመምረጥ ተስማሚ የእርከን ዓይነቶችን መለየት እና የገቢ ምንጭ ሊያስገኙ የሚችሉ ተግባራት ተቀናጅተው የሚከወኑበት ሁኔታ በማጤን ኅብረተሰቡ የሚጠቀምበትን መንገድም የሚያሳይ ነው።

በዚህም ሳቢያ በየአካባቢው ጠፍተው የነበሩ የእጽዋትና የእንስሳት ዝርያዎች በመመለስ ላይ ይገኛሉ። ቴክኖሎጂው ለአካባቢ ጥበቃ ከሚያደርገው ጉልህ ድርሻ ባሻገር፤ ከግብዓት አቅራቢዎች ጋር የአቅርቦት ትስስር በመፍጠር በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያደርግ ነው። ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታው አስተማማኝ በመሆኑም ለቴክኖሎጂው ዘላቂነት ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ነው፡፡

የተጎዱ መሬቶች መልሰው እንዲያገግሙ ለማድረግ የተለያዩ ሀገር በቀል ዛፎችን መትከል ዋነኛው አማራጭ ነው። ለዚህም በርካታ የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎችን በብዛት መጠቀም ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ አገር በቀል ችግኞች በመልማት ላይ ናቸው። ችግኞችን በማልማትና ደኖችን መንከባከብ በመቻሉ የአገሪቱ የደን ሽፋን ከነበረበት ከፍ ማድረግ ተችሏል። ይህ ታላቅ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂው አንዱ አካል ነው። ይህን ተግባር አጠናክሮ መቀጠል እጅግ አስፈላጊ ነው።

በአካባቢ ጥበቃ ስራ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ መሆን በመቻሉ፤ አሁን ላይ የአካባቢ ነዋሪዎችና አርሶና አርብቶ አደሩ ለአካባቢ ጥበቃ ስራ ጊዜ ሰጥቶ ሁሉም በነቂስ ወጥቶ በመተግባር ላይ ይገኛል። በዚህም በበርካታ የአገራችን አካባቢዎች በተከናወኑ የተፋሰስ ልማት ስራዎች በርካታ ወጣቶችና ሴቶች ተጨማሪ የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂን በመጠቀም በአካባቢ ጥበቃ እያከናወነች ያለችው ተግባራ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ ባሻገር፤ ለአካባቢ ተስሚ መሆኑን ተጨባጭ የተገኙ ውጤቶች ህያው ምስክር ናቸው፡፡

ሀገሪቱ ለተያያዘችው የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ለዘመናት ትታወቅበት ከነበረው ድህነት የምትላቀቅበት ወሣኝ ጉዳይ ነው። ይህን በመረዳት ለአካባቢ ጥበቃ ዘርፉ ጠቃሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለህብረተሰቡ በማስተዋወቅና የተጀመረውን የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ልማት ስራ በመገንዘብ ተግባሩን አጠናክረው መቀጠል አለበት፡፡

ዓለማችንን ለኑሮ ምቾት በማድረግ የአካባቢ ጥበቃ ተግባራትን በማስፋት፤ የተፈጥሮ ሀብት በመንከባከብ፣ በአግባቡ መጠቀምን ከወዲሁ ማሰብ ይኖርብናል። ለዚህ የዓለም ሀገራት የተለየ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ነው። እኛም ከተቻለ ደኖችን ወደ ነበሩበት መመለስ፤ ካልሆነም ጫናዎችን በመቀነስ የብዝኃ ሕይወት ሀብታችንን ከጥፋት መታደግ ይገባናል።

ከዚህ አንጻር በተለይም ከባለፈው ዓመት ጀምሮ አርንጓዴ ሌጋሲ በሚል በመላ አገሪቱ እየተከናወነ የሚገኘውና በዚህም በጀት ዓመት አጠናክሮ ለማስቀጠል እየተደረገ ያለው ርብርብ ፋይዳው ከአገራችን አልፎ ለዓለምም የሚተርፍ ነው።

ለመትከሉ ብቻ ሳይሆን ለመንከባከብና ለመጽደቅ ልዩ ትኩረት በመስጠቱም የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አህመድ በተምሳሌትነት ችግኞችን የመንከባከቡ ሥራ ሲሰሩ ታይቷል። የሚመከለከታቸው አካላትም ለጉዳዩ በሰጡት ትኩረት ባለፈው ዓመት ከተተከሉት ችግኞች ከ84 በመቶ በላይ መጽደቃቸውን የግብና ሚኒስቴር በቅርቡ ገልጿል።

ከላይ እንደገለጽነው ይህ ሥራ ፋይዳው ለምድርም ሁሉ የሚተርፍ ነውና ከዚህም በበለጠ ሁኔታ ተጠናክሮ የሚቀጥል ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በዚህ በጀት ዓመትም ከአምስት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ለመትከል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንና ለዚህም አስፈላጊ የሆኑ ችግኞች እየተሰናዱ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አህመድ በቅርቡ አስታውቀዋል።

በዚህ ሥራ ልዩ ትኩረት የተደረገው ደግሞ ከሚተከሉ ችግኞች 80 በመቶው እንደ ማንጎ አፕል ፓፓያና አቦካዶ ያሉ ፍራፍሬዎች እንዲሆኑ መደረጉ ላይ ነው። ይህም በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደሚለው ብሂል አንድም ከዛፎቹ የሚገኘው አካባቢያዊና የአየር ጸባይ ጠቀሜታ እንዳለ ሆኖ በምግብ ዋስትናና የኢኮኖሚ አቅምን ለማጠናከር የሚኖረው ጠቀሜታ እጅጉን ትልቅ ነው፡፡

በአጠቃላይ የአሁኑ ትውልድ ጠብቆ የሚያቆየው ምድር ነውና፤ የመጪው ትውልድ ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን፤ ኃላፊነትን በመወጣት እጅግ አስፈላጊ ተግባራ መፈጸም የሁሉም ድርሻ ነው። አካባቢን ጤናማ በማድረግ፤ ደኖችን በመንከባከብ፤ ብዝኃ ሕይወት በመጠበቅ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገርና ለመጪው ትውልድ የበለጸጉ ሆነው እንዲቀጥሉ ከወዲሁ መትጋት ይጠበቅብናል፡፡ እንደ አስተዳደራችን እየተሰራ ያለውን የአረንጓዴ ልማት ስራ ላይ በተለይ ወጣቶች ትልቅ ሀላፊነት ይጠበቅባቸዋል በማለት ሀሳቤን እቋጫለሁ፡፡

# የባንኮች ጉዳይ......

በኤደን ሳሙኤል

ቁጠባ ዛሬ ላይ ሆነን ነገን በማሰብ ከምናገኘው ገቢ በተወሰነ መጠን ወይም መቶኛ ቀንሰን የምናስቀምጠውና ለፍጆታ የማናውለው ገንዘብ ነው፡፡ ቁጠባ ለነገ የተሻለ ህይወት፣ ለእርጅና ዘመን፣ ወደፊት ለሚያጋጥመን የገንዘብ እጥረት፣ ለልጆቻችን የወደፊት የከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት፣ ሊያጋጥሙን ለሚችሉ አደጋዎች መቋቋሚያ ወዘተ. ፍላጎቶቻችን ሁሉ ለመጠቀም እንድንችል ዛሬ የምናስቀምጠው ገንዘብ ነው፡፡

ሰላም ጤና ይስጥልኝ ውድ አንባቢያን እንዴት ከርማቹሀል.... ሳምንታችሁ በመልካም ሁኔታ እንዳለፈ ተስፋ እያደረኩ ዛሬ በቢዝነስ አምዳችን ወደ እናንተ ለማድረስ ወደተዘጋጀሁበት ርዕሰ ጉዳይ በቀጥታ አመራለሁ፡፡ ውድ አንባቢያን ዛሬ በቀጥታ የማወራችሁ ስለቁጠባ አስፈላጊነትና ጥቅም አይደለም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ዙሪያ በበርካታ የሚዲያ አውታሮች በዙ ስለተባለ ማለት ነው፡፡

በዚህም ወደእናንተ ለማድረስ የወደድኩት ሃሳብ ጠቅለል ባለ መልኩ ስለቁጠባ ጥቅምና፣ በስፋት ደግሞ ስለባንኮች ወሰን የለሽ የአካውንት ክፈቱና ቆጥቡ ጥያቄ ነው፡፡ እዚህ ጋር ግን ልብ ሊባል የሚገባው መቆጠብ አስፈላጊ ሆነ ሳለ ባንኮች ግን ይህንን የቁጠባ ባህል የሚያስፋፉበት መንገድ እንዴት ነው የሚለውን እንታዘባለን፡፡

አንዳንድ ፀሐፊዎች ቁጠባ ወደ ኢንቨስትመንት ካልገባ ቁጠባ ሊባል አይችልም ይላሉ፡፡ በእርግጥ ቁጠባ የኢንቨስትመንት መሰረት ነው፡፡ የምንቆጥበው ገንዘብ በቀጥታ ወደ ኢንቨስትመንት ማዞር ከቻልን ማለትም የንግድ ሥራ ልንጀምርበት ከቻልን የወደፊት ገቢያችንን ስለሚያሳድግልን ኑሮአችን ተሻሻለ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ቁጠባ ለኢንቨስትመንት ብቻ ሳይሆን ከላይ የገለጽናቸውን የወደፊት እቅዶቻችን ለማሳካትም ሆነ ለሚያደጋጥሙን ችግሮች መውጫነት ሊያገለግለን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ቁጠባ በተገቢው ቦታ መቀመጥ ከቻለ እኛ ወደ ንግድ ሥራ ማስገባት እንኳን ባንችል ሌሎች ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ቁጠባን ኢንቨስትመንት ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ቁጠባን በተገቢው ቦታ እናስቀምጥ ስንል በባንክ ወይም በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ማስቀመጥ እንዳለብን ለማመልከት ነው፡፡ ቁጠባን በቤት ውስጥ ማስቀመጥ እንደ ቁጠባ አይቆጠርም፡፡

ምክንያቱም አንደኛ፣ ገንዘብ እጃችን ላይ ባጣን ቁጥር በትንሽ በትንሹ እየቆነጠርን ስለምንጨርሰውና በቋሚነት ማስቀመጥ ስለማይቻል፣ ሁለተኛ በቤት ውስጥ ማስቀመጥ ለስርቆትና ሌሎች አደጋዎች የተጋለጠ ከመሆኑም በላይ በእርጥበትና በሌሎች ነገሮች ሊበላሽ ይችላል፣ ሶስተኛውና ዋነኛው ግን ቁጠባ በባንክ ካልተቀመጠ ሌሎች ገንዘቡን ሊጠቀሙበት አይችሉም፣ እኛም ባንክ በማስቀመጥ የወለድ ተጠቃሚ መሆን ስንችል ቤት ውስጥ ካስቀመጥን ወለድ ልናገኝበት አንችልም፡፡ የቁጠባ ዋናው ዓላማ አንዱ ሊጠቀምበት ያልቻለውን ገንዘብ ሌላኛው በብድር ወስዶ እንዲጠቀምበት ማድረግ በመሆኑ ቁጠባ በምንም አይነት መልኩ በቤት ውስጥ መደረግ የለበትም፡፡

አንዳንዴ አነስተኛ የገንዘብ መጠን በየቀኑ መቆጠብ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ኑሮአቸው በእለት ገቢ ላይ የተመሰረተና በትናንሽ የንግድ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ሰዎች በእለት ከሚያገኙት ገቢ ላይ የተወሰነ ገንዘብ በመቀነስ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ አነስተኛ የገንዘብ ሳጥን ውስጥ ሲያጠራቅሙ ይታያሉ፡፡ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ሳጥናቸውን ሲከፍቱ ጠቀም ያለ ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ በዚህ ገንዘብም ንግዳቸውን ሲያስፋፉ፣ወላጆች ለልጆቻቸው የትምህርት ቤት ክፍያና ዩኒፎርም ሲያሰፉ፣ ወጣቶች አጠራቅመው ቤተሰባቸውን ሲረዱ እና ሌሎች በርካታ ተግባራትን ሲያከናውኑ እንመለከታለን፡፡ ይህ የቁጠባ ዘዴ ጥሩ ቢሆንም በተወሰነ የጊዜ ገደብ እየከፈትን ጠርቀም ያለውን ገንዘብ ወደ ባንክ ብናስገባው ይበልጥ ተጠቃሚ እንሆናለን፡፡

ቁጠባ ለሥራ ፈጣሪዎች እጅግ ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ሥራ ፈጣሪዎች አዲስ የንግድ ሠራ ሲጀምሩ ህጋዊ የሰውነት



መብት የማግኘት እና ግብር የመክፈል መብትም ግዴታም እንዳለባቸው ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ቁጠባ ግደታ ባይሆንም የሥራ ፈጣሪዎች የግድ መቆጠብ አለባቸው፡፡ ቁጠባ ለሥራ ፈጣሪዎች የሚያስፈልጋቸው፣ አንደኛ የንግድ ሥራቸውን ለማስፋፋትና በገበያው ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን የንግድ ሥራቸው እያደገ መሄድ ያለበት በመሆኑ ነው፡፡ የንግድ ሥራቸውን ለማሳደግ ደግሞ ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ይህንን ተጨማሪ ገንዘብ ሊያገኙ ከሚችሉባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው ቁጠባ ነው፡፡ ሁለተኛ ራዕያቸውን ዕውን ለማድረግ ስለሚረዳቸው ነው፡፡ የሥራ ፈጣሪዎች የትልልቅ ራዕይ ባለቤቶች ናቸው፡፡ በራዕያቸው አንዱ ከጥቃቅን የንግድ ሥራ በመነሳት ትልቅ ፋብሪካ ማቋቋም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ማድረግ የሚቻለው ቁጠባን እንደ ግዴታ በመውሰድ ሳናቋርጥ መቆጠብ ከቻልን ነው፡፡ ሶስተኛ ለሌላ አዳዲስ የሥራ ፈጠራ ፍላጎታቸው የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ሊያገኙ የሚችሉት ዛሬ ከሚያገኙት ገቢ ላይ መቆጠብ ከቻሉ ነው፡፡ አራተኛ የቁጠባ ባህል መዳበር ያለበት በሥራ ፈጣሪዎች ብቻ ሳይሆን በሁሉም ዜጎች ዘንድ በመሆኑ የሥራ ፈጣሪዎች ለሌሎች ሞዴል ሆነው መታየት ስላለበባቸው ነው፡፡

ቁጠባ በሀገር ደረጃ ሊያድግ የሚችለው ሁሉም ዜጎች የሚያደርጉት ቁጠባ በድምር ሊያድግ ከቻለ ነው፡፡ በአንድ ሀገር ቁጠባ ማደግ ከቻለ ኢንቨስትመንት ይስፋፋል፡፡ ኢንቨስትመንት ያለቁጠባ በአንድ ሀገር ውስጥ ሊመጣ አይችልም፡፡ ምናልባት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ሊኖር ይችላል፡፡ ይህም ቢሆን በሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ካልታገዘ የአንድን ሀገር ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ በውጭ ባለሃብቶች እጅ እንዲገባ ሥለሚያደርገው የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

ስለሆነም እያንዳንዱ ዜጋ ያለችውን አነስተኛ ገንዘብም ቢሆን በመቆጠብ ራሱን ተጠቃሚ ከማድረጉም በላይ ለሌሎች ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሥራ እድል እንዲፈጠርና የሀገር ኢኮኖሚ እንዲያድግ የበኩሉን እገዛ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በሀገራችን በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቤተሰቦች ስለ ቁጠባ ጠቀሜታ ቢረዱም “የምናገኘው ገቢ አነስተኛ ስለሆነ ከዚህች ላይ እንዴት መቆጠብ እንችላለን? ይላሉ፡፡ እውነታው ግን መቆጠብ ያለብን ከዚህችው አነስተኛ ከሆነችዋ ገቢያችን ላይ መሆኑ ነው፡፡

እዚህ ጋር አንባቢያን አንድ ታሪክ ላጫውታችሁ የመንግስት ተቀጣሪ የሆነችው አንድ ጓደኛዬ በመስሪያ ቤታችን ስላለው የቁጠባና ብድር የኀብረት ሥራ ማህበር አስረዳኋትና በብዙ ድካምና ልፋት የደሞዟን አምስት ከመቶ እንዲቆጥብ አሳመንኳት፡፡ ደመወዜ አነስተኛ ስለሆነች እንዴት ነው ከዚህች የምቆጥበው የሚል ከላይ የገለጽኩትን አይነት ጥያቄ ማንሳቷነው ነገሩን ከባድ ያደረገው፡፡ አጋጣሚ ሆኖ ከስምንት ወራት ቆይታ በኋላ እድገት በማግኘቷ ደሞዟ ከ60% በላይ አደገላት፡፡ በዚህ ጊዜ ቢያንስ ቁጠባዋን ከአምስት በመቶ ወደ አስር በመቶ እንድታሳድግ ነገርኳት፡፡

እሷ ግን ያችው አምስት ከመቶዋ ለዚያውም በቀድሞው ደሞዟዋ ስሌት ተወስኖ ለሁለትና ሶስት አመታት በዚሁ ቀጠለ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እድለኛ ሆና የጋራ መኖሪያ ቤት እጣ ደረሳት፡፡ በዚህ ጊዜ ከማህበሩ ብድር ለመጠየቅ ስትመጣ የቆጠበችው ገንዘብ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ የሚፈልገውን ያህል ብድር ልታገኝ አልቻለም፡፡ ከሌላ ምንጭ ገንዘብ ለማግኘት ቢሞክርም የሚቻል አልሆነም፡፡ የነበረው አማራጭ የደረሰውን የቤት እጣ መተው ነበር፡፡

ከዚህ የምንረዳው ቁጠባ ለነገ ማንነታችን እጅግ ወሳኝ እንደሆነና ቁጠባን የህይወታችን አንዱ አካል አድርገን ማየት ካልቻልን የወደፊቱ ጊዜ የእኛ አንዳይሆን ካሁኑ እየወሰንን እንደሆነ ነው፡፡ ገንዘብ ስናገኝም ፍላጎታችን በዚያው ልክ እያደገ ስለሚሄድ ቁጠባን መጀመሪያውኑ ባህላችን አድርገን መሄድ ካልቻልን የፈለገውን ያህል ገቢያችን እያደገ ቢሄድ ልንቆጥብ አንችልም፡፡ ስለዚህ ካለችን አነስተኛ ገንዘብም ቢሆን መቆጠብ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉም ሰው ግንዛቤ ሊወስድ ይገባል፡፡ ታዲያ በተለይ አሁን ባለንበት ዘመን ቁጠባን በተለያዩ አማራጮች መቆጠብ እንደምንችል ይታወቃል፡፡ ከነዚህ አማራጮች መካከል ደግሞ በዘመናዊ መልኩ በባንኮች መቆጠብ የባንክ ደብተር በማውጣት በቀጥታ የባኪንግ ሲስተም ውስጥ በማምራት ተጠቃሚ መሆን ነው፡፡

በነገራችን ላይ ውድ አንባቢያን የኢትዮጵያ የባንክ ታሪክ የሚጀምረው በ1887 ዓ.ም. እንደሆነ አቶ በላይ ግደይ “ገንዘብ፣ ባንክ እና መድኅን በኢትዮጵያ” በሚለው መጽሐፋቸው አስፍረዋል፡፡ በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በተጠቀሰው ዓመት የተቋቋመው የመጀመርያው ባንክ ስራ የጀመረው በ1901 ዓ.ም. መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ መረጃው እንደሚያሳየው 126 ዓመት ያስቆጠረው የባንክ ስርአት እድገት የእድሜውን ያህል እንዳልሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡

የባንክ ተጠቃሚው ቁጥር አሁንም እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ የባንኮቹ ቁጥርም ኢኮኖሚው እና የሕዝቡ ብዛት ከሚፈልገው አንጻር አነስተኛ ስለመሆኑ የሚናገሩ ባለሙያዎች አሉ፡፡ አሁን ያሉን ባንኮች ልዩነት የስም ብቻ ነው የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች ደግሞ ገበያው ላይ ያሉት ባንኮች በብድር አሰጣጥ፣ በወለድ ምጣኔ፣ በደንበኛ አያያዝ እና ሌሎች ጉዳዮች ያላቸውን ተመሳሳይነት ይተቻሉ፡፡ ተጠቃሚው እንደ ፍላጎቱ የሚቀላቀላቸው ባንኮች ባለመኖራቸው ባንኮቻችን ምርጫ እንጂ አማራጭ የላቸውም የሚል ሐሳብ አላቸው፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከቁጥራቸው መጨመር ጋር ተያይዞ ባንኮች ልዩ ልዩ አሰራሮችን መከተል ጀምረዋል፡፡ ደንበኛ ወደ እነርሱ እንዲሄድ መጠበቃቸውን አቁመው ወደ ደንበኛው የሚያስኬዷቸውን አማራጮች እየተከተሉ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ከላይ እንዳነሳነው የባንኮች የውስጥ አሰራር ሁሉ ተመሳሳይነት ቢኖረውም ከዚህ በፊት ከነበረው አሰራር ግን የተለየ ነው፡፡

ለዚህ እንደ ምሳሌ የውጭ ሐገር ገንዘቦችን ለሚመነዝሩ የተለያዩ ማበረታቻዎች መስጠት፣ ቆጣቢዎችን በዓመታዊ እጣ መሸለም፣ ለቆጣቢ ሴቶች አበረታች ወለድ መክፈል፣ ከወለድ ነጻ አገልግሎት መስጠት፣ ደንበኛው የሚገኝባቸው አካባቢዎች በመገኘት አካውንት ማስከፈት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ደንበኛው ባንክ መሄድ ሳያስፈልገው ባንኮቹ ወደ ንግድ ተቋሙ ሰራተኞች ልከው እለታዊ ገቢ የሚሰበስቡበት፣ ከስራ ቀንና ሰዓት ውጭ የሚሰሩበት፣ በስልክ ትእዛዝ ጥሬ ገንዘቡን ለደንበኛው የሚያቀብሉበት አሰራሮች ደግሞ ዛሬ ላይ እንደ ቅንጦት እየተቆጠሩ ያሉ ጥቂት ባንኮች የሚከተሏቸው አሰራሮች ናቸው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ትኩረት መንገድ ላይ፣ በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቤቶች አካባቢ የባንክ አካውንት ለማስከፈት የሚጥሩ ባንኮችን የሚመለከት ነው፡፡

በድሬዳዋ ከተማ ብቻ ሳይሆን መዲናዋን አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎችም የሐገሪቱ ከተሞች እየተለመደ የመጣው በመንገድ ላይ ወይም በስራ ቦታ የባንክ አካውንት የማስከፈት ሂደት እንዳማረረው የነገረን ወጣት አቡበክር ሁሴን ይባላል፡፡ ነዋሪነቱ ድሬደዋ ከተማ ኮኔል ሰፈር አካባቢ ነው፡፡ አስተያየቱን የጀመረው አንድ አጋጣሚውን በማስቀደም ነው፡፡

‹‹አንድ ጊዜ ገንዘብ ለማውጣት ባንክ ሄድኩ፡፡ የባንክ ቡኬን ስላልያዝኩና ቁጥሩን በቃሌ ስላላወቅኩት በስልክ ቁጥሬ አውጡልኝ አልኩ፡፡ እሺ ብለው ሲያወጡልኝ ግን በእኔ ስልክ እና ስም 3 አካውንት ተገኘ፡፡ መቼ እንዳወጣሁት ለማወቅ ብዙ ማስታወስ ነበረብኝ›› ብሎናል፡፡ ሁኔታው እንዴት እንደተፈጠረ ሲያስረዳም “የአንድ ባንክ ቅርንጫፍ ቢሮ ለአገልግሎት ያመራ ደንበኛ የተመሳሳዩ ባንክ ደብተር ቢኖረው እንኳን የራሳቸው ቅርንጫፍ ላይ ድጋሚ እንዲያወጣ ያስገድዱታል፡፡ ይህ ደግሞ ሰዎች ሳያስቡት እና ጉዳያቸው እንዲያልቅላቸው ብቻ አካውንት እንዲከፍቱ አድርጓል” ሲል ሐሳቡን ነግሮናል፡፡

“በአሁኑ ሰዓት ሁሉም ባንኮች በሚባል ደረጃ በየአካባቢው እየዞሩ ሰዎች የባንካቸው ደንበኛ እንዲሆኑ ይቀሰቅሳሉ፡፡ በማስረዳት እና በማባበል ጭምር ባንክ ደብተር ያስከፍታሉ፡፡ ይህ አሰራር ለባንኮቹም ሆነ ለደንበኞች የሚሰጠው ጠቀሜታ እንዳለ አይካድም፡፡ በልዩ ልዩ ምክንያት ባንክ መሄድ ያልቻለው ደንበኛ ካለበት ቦታ ሳይንቀሳቀስ የባንክ አገልግሎት የሚያገኝበትን እድል ያመቻችለታል፡፡

ባንኮችም በአጭሩ የደንበኞቻቸውን ቁጥር በረዥሙ የተቀማጭ ገንዘባቸውን መጠን ከፍ ያደርጉበታል፡፡ በተቃራኒው ባንኮቹ ይህንን መሰሉ ተደጋጋሚ ውትወታ ተጠቃሚውን ሊያሰለች እንደሚችል የዘነጉት ይመስላል፡፡” በማለት የሰጠንን አስተያየት ደምድሟል፡፡ የተሰላቸውን ተጠቃሚ የሚወተውቱት የባንክ ባለሙያዎችም ጫና ውስጥ ናቸው፡፡ በራሳቸው ገንዘብ መንገድ ላይ ላገኙት ተጠቃሚ አካውንት የሚከፍቱ ባለሙያዎች እንዳጋጠሟቸው ለዚህ ጽሑፍ ያነጋገርናቸው የድሬዳዋ ከተማ ነዋሪዎች ነግረውናል፡፡

“አንድ ሰው በይሉንታም ይሁን ጭቅጭቁን ጥላቻ እስከ አምስት የተለያየ አካውንት ይኖረዋል በአምስቱም አካውንት ግን ይጠቀማል ማለት ከባድ ነው” ያለችን ደግሞ ራሄል ተክሉ ነች፡፡ የምትሰራበትን ቢሮ በቀየረች ቁጥር የባንክ አካውንት እንደምታወጣ የምትናገረው ራሄል ባንኮች በጋራ የሚሰሩበት አሰራር ቢኖር የማይጠቀሙበትን የባንክ ደብተር ከመሰብሰብ እንደሚያድን ሐሳቧን ሰጥታለች፡፡

የተለያዩ የንግድ ተቋማትንና ድርጅቶችን ተዘዋውረን ባነጋገርንበት ወቅት በባንኮች የአካውንት ክፈቱ ውትወታ እንደተማረሩ የሚገልፁ ብዙዎች ናቸው፡፡ በድሬዳዋ ከተማ ኮፒ ቤት ያላት ናርዶስ እሸቱ የተባለች ወጣት እንደገለፀችው በሳምንት ከሦስት ጊዜ በላይ የተለያዩ ባንኮች ሰራተኞች የስራ ቦታዋ እየመጡ አካውንት እንድትከፍት ይጠይቋታል፡፡

ይበልጥ ያስገረማት ነገር ደግሞ ልጆቹ “አልፈልግም” ወይም “አለኝ” የሚል መልስ ሲሰጣቸውም ለመሄድ ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ጉዳይ ነው፡፡ በድሬዳዋ ከተማ ነምበርዋን ሰፈር የምትኖረው ህይወት የፀጉር ቤት ባለቤት ነች፡፡ “ከደሀው ሕብረተሰብ ላይ ሀምሳ ብር መቀማት ነው የተያዘው፡፡ ሰው በሚያተርፈው ልክ በአንድ ባንክ ቤት ቢቆጥብ በቂ ነው፡፡ በይሉንታና በትውውቅ የማንጠቀምበትን አካውንት እንድንከፍት ያደርጉናል ስትል ምሬቷን ታብራራለች፡፡

ሁኔታው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የመግቢያ ሰሞኖች ላይ እንደሚባባስና ተማሪዎችም ባለማወቅ የማይጠቀሙባቸውን የባንክ ደብተሮች እንደሚሰበስቡ አጫውታናለች፡፡ ዓየሁ ሙላቴ የተባለች ተማሪ የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ የመጀመርያ ዓመት ተማሪ ስትሆን ሁለት አካውንት ሳትፈልግ እንደከፈተች ገልጻ በተለይ ልክ እንደ እርሷ ብዙም የባንክ አገልግሎት ካልተስፋፋበት አካባቢ የሚመጡ አዳዲስ ተማሪዎች እንደሚደናገሩና ላልሆነ ወጪ እንደሚዳረጉም ገልፃልናለች፡፡

# ወልደ ህይወት ! !

በዘመድ ቢሆነኝ

በዓለም የፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ይዘው የሚገኙት አውሮፓዊያን ሲሆኑ በተለይ ደሞ የሀገረ ግሪክ ፈላስፎች ናቸው፡፡ ከነሱም በተጨማሪ የመካከለኛው ምስራቋ ሀገር እስራኤል (አይሁድ ፈላስፎች) ግንባር ቀደም የሚባሉ ፈላስፎችን ለዓለም አበርክታለች(ማርክስ ፤ ኒቼ...)፡፡ ወደ ሩቅ ምስራቅ ሀገራት ስንመጣ ህንድ እና ቻይናም ለዓለም ያበረከቱት የፍልስፍና አስተዋፅኦ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በተለይም <existential> የተባለውን የፍልስፍና ዘይቤ ለዓለም በማበርከት ባለውለታ ናቸው፡፡

ፍልስፍና በታሪኩ በብዙ አሳቢያን የመቀንቀኗን ያኽል ፤ የሰውን ልጅ ቀልብ ገዝታ ብዙ ዘመናትን የመቆየቱን ያኽል በርግጥም ዓለምን በተለየ እና በሚያበለፅግ መንገድ እንድናያት እና የፍልስፍና ፍሬ በሆኑት ሀሳቦች እየታገዝን ዓለምን እንድንለወጥ ታላቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በተለይ ከነሶቅራጥስ ዘመን አንስቶ እስከ እነ ሲግመንድ ፍረበድ ዘመን ድረስ ፍልስፍና ተፅዕኖዋ ታላቅ የሚባል ነበር፡፡ ነገር ግን ሳይንስ እያደገ ከመምጣቱ ጋር ፤ ቴክኖሎጂዎች እየረቀቁ ከመምጣታቸው ጋር ተያይዞ የፍልስፍና ዋጋ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ዓለም ከ<ሀሳብ> ይልቅ <ቴክኖሎጂ> ላይ በማተኳሯ ፍልስፍና የቀደሞውን ዝናዋን አጥታለች ባይባልም ቀንሷል፡፡

የፅሁፌ ነጥብ ስለፍልስፍና ታሪክ እና የሌሎችን ሀገራት ተሳትፎ ለማተት ሳይሆን በፍልስፍና ታርክ ውስጥ የሌሎችን ሀገር ተሳትፎ አይተን ስናበቃ "እኛስ"እንደ ሀገር ማን ነበረን? በድፍረት የማህበራዊ ፤ የሀይማኖታዊ ፤ የፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ግድፈት በአመክንዮ (በፍልስፍና ወይም በሀሳብ) የሞገተ አሳቢ ነበረን ወይ የሚል ጥያቄ አንስቶ ለዚሁ መልስ መስጠት ነው የፅሁፌ ነጥብ፡፡በዚህም ታሪካዊ መፅሐፍትን ለማሰስ ሙከራ አድርጊያለሁ፡፡


ይህ ነው የሚባል መረጃ ማግኘት ግግ አልቻልኩም፡፡ ሆኖም ግን ከትልቅ የስንዴ ማሳ ውስጥቢያንስ አንዱ ፍሬ ማበቡ አይቀርምና ከብዙ ፍለጋ በኋላ በቅርቡ ታትሞ ለንባብ የበቃው <ጥበብ ከጲላጦስ ቅፅ ሁለት> መፅሐፍ ውስጥ ልብ የሚሞላ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነች ፍልስፍናዊ ታሪክ ለማግኘት በቃሁ፡፡ የኔ ሀተታ እዚህ ላይ ይቁምና ከመፅሐፉ ወደወሰድኩት ፅሁፍ ላምራቹህ።

መፅሐፉም እንዲህ ይቀጥላል፡- ወደ ሀገራችን የፍልስፍና አስተሳሰብ ተመልሰን እነሆ ወልደ ህይወትን አገኘነው፡፡ ወልደ ህይወት የኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርአያዕቆብ ደቀ መዝሙርና ተማሪ በመሆን ለ59 ዓመታት ከስሩ ያልተለየ ድንቅ አሳቢ ለመሆኑ በመምህሩ ዘርአያዕቆብ መፅሐፍ ላይ ጨምሮ ያበረከተውና የእሱን አስተሳሰብ በስፋት የታየበት ሐተታ ይመሰክራል፡፡ <ሐተታ ዘርአያዕቆብ ፍልሱፍ> በሚለው የመምህሩ መፅሐፍ ውስጥ ተተንትኖ የቀረበልንን የወልደ ህይወት ሀሳብ ስናነብ ደግሞ በዋነኛነት የሐተታው ዓላማና ግብ ሆኖ የምናገኘው <የመጨረሻው መልካምነት> ምን እንደሆነ ነው፡፡

"እኔም ምትኩ የተባልኹ ወልደ ህይወት የመጨረሻው መልካምነት እንድታውቁ ብዬ ከመምህሬ መፅሐፍ ላይ ይኽን ትንሽ ጨመርሁ" የሚለን ወልደ ህይወት መምህሩ የነበረው ዘርአያዕቆብ በ68 ዓመቱ ፋሲለደስ ሞቶ ዮሐንስ ሲነግስ በፃፈው መፅሐፍ ላይ የበኩሉን ጨምሮ እንዳበረከተ ይነግረናል፡፡

እንግዲህ ወልደ ህይወት ለ59 ዓመታት ከዘርአያዕቆብ ስር ሆኖ የተማረውን <ለኢትዮጵያ ልጆች ዕውቀትና ተግሳፅ> እንዲሆናቸው አስቦ መፃፉን ከጅምሩ ሲነግረን የፍልስፍናም ዋነኛ ዓላማ ይኸው ነውና ዕውቀትና ተግሳፅ ይተርፈን ዘንድ በዚህ ዘመን እንኳን የተደረሰበት ከማይመስለው የላቀ አስተሳሰብ በመጠኑ እንቆነጥራለን፡፡

ወልደ ህይወት በአስተሳሰቡ እንደ መምህሩ ዘርአያዕቆብ በዘመኑ ሰዎች ሀይማኖትን ለማስካድ እንደተነሳ ሰው መቆጠሩ ያልቀረለት ቢሆንም እሱ ግን ሐተታውን ሲጀምር እንዲህ ይለና፡-"ሁሉን በፈጠረና በያዘ ሁሉን በሚጠብቅና በሚመግብ ከዓለም በፊት የኖረና ያለ እስከ ዘላለምም የሚኖር ብቻውን በፍፁም ህልው የሆነ ለእርሱ ታላቅነትም ዳር ድንበር የሌለው በእግዚአብሔር ስም እፅፍላሁ!!" ይለናል፡፡ ወልደ ህይወት መፅሐፉን እንዲህ ብሎ መጀመሩ አስተሳሰቡ




አንዳች ግጭት በእሱ ዘመንም ሆነ በኋላ ከሚመጣው ትውልድ ጋር ቢስያነሳ ከአምላኩ ሀሳብ ጋር የሚጋጭ ጉዳይ አለማንሳቱን እንድንረዳለና በዚህም ምክንያት ድፍረት መቋጠሩን የዘየደው መስሎናል፡፡

መምህሩ ዘርዓያዕቆብ "ፈርቼ የደበቅሁትን እውነት የማይፈራ ይፃፈው" በማለት ያስፈረውን ሐሳብ ይዞ የእሱ ፍርሃት ግን አምላኩ ብቻ የመሆኑን ጋሻ አስቀድሞ አንስቶ ይመጣልናል፡፡ ይኸም ብቻ አይደለም፡፡ መፅሐፉ በስሜት ተገፋፍቶ ያለዕውቀት በመነዳት የመሰለውን የሚሞነጭር ስራ ፊት አልያም ዕብድ ያቀረበው ሳይሆን <ጥበብና ምርመራ እንዲሁም ተግሳፅና ፍልስፍና የደረሰው አንድ ትልቅ የሀገራችን መምህር ስሙ ወልደ ህይወት የተባለ> እንደፃፈልን እንድነረዳም ያስጠነቅቀናል፡፡

ወልደ ህይወት የመፅሐፉን ሐሳብ ከማስፈሩ በፊት እንደሚነግረን ያስፈረልን ሐሳቦች በራሱ ምርምራ መልካም መሆኑንም ከለየ በኋላ የፂፈልን እንጂ ከሰው አፍ የሰማውንና ከሰው ትምህርት የተቀበለውን <ምንም እንደማይፅፍ> ነው፡፡

እንዲያውም በመፅሐፉ ያስፈራቸው ሐሳቦች በብዙ ፀሎትና ምልጃ እውነትን እንዲያሳየው እግዚአብሔርን ከለመነ በኋላ የመረመረውንና <የዓወቀውን> ለመሆኑ ነግሮን ከዚህ በኋላ "እውነት የመሰለኝን እፅፍአለሁ ፤ ይኸን መፅሐፌን የእምታነበው ወንድሜ ሆይ እኔም እንዳልዋሽ በእሚከለክለኝ በትልቅ የእግዚአብሔር ፍርሀት እንደፃፍኩት እወቅ" በማለት ሐሳቡን በዘመኑም ሆነ በኋላ የሚመጣው ትውልድ ዘንድ ሊፈጥር የሚችለውን <ቁጣ> ማለዘቢያ የመሰለ ሐሳብ ያሰፍራል፡፡

ይሁኑና ወልደ ህይወት ሐሳቡ በሰዎች ዘንድ ቁጣ ሊያስነሳበት እንደሚችል ደሞ ያጣው አይመስልም፡፡ ወረድ ብሎ ፡-"ነገር ግን የሰው መፍራት የለብኝም ፤ የፊታቸውንም ምንም አልአፍርም፡፡ ከንቱና ሐሰትን ከእሚአስተምሩና ከእሚፅፉም ጋር በማናቸውም ስራ አልተባበርም፡፡ እውነትን አንተ ብቻህን ነህ የአወቅሀትን? ከአንተ በቀር ሁሉ አልአወቅዋትና ወደድዋት እንጂ እኔ ብቻዬን አልአወቅኅትም፡፡ ነገር ግን የሰውን ስድብና የግሩም ጨለማ ከሆነ ማህበራቸው መባረርን ስለፈሩ በግልፅ ማስተማርን አልደፈሩም" በማለት በአስተሳሰቡ ምክንያት አንዳች ቁጣና ውግዘት ቢደርስበት እንደማይፈራ ይነግረናል፡፡ እንዲያውም ባለመመርመራቸውም ያላወቁ በመሆናቸው የሰሙትን ብቻ አምነው የተቀበሉ "ሀይማኖተኛ ናቸው" ይለናል፡፡

ወልደ ህይወት በራሳቸው መርምረው ለደረሱበት እውነትና ዕውቀት ይልቅ የነገሯቸውን ብቻ አምነው ስለተቀበሉ ሀይማኖተኞች ሲነግረን እንዲህ ይላል ፡- "የቀሩት ሰዎች ግን ፅድቅ ሊሆን ሐሰት ሊሆን እንዲአውቁ አልመረመሩምና አልአወቁም፡፡ አለ ምርመራ ከፊተኞቻችው የሰሙትን አምነው ተቀበሉ፡፡ ስለ ይህም የአይሁዱ ልጆች አስላም ሁኑ፡፡ እነ እርሳቸው የአባቶቻቸው ልጆች ናቸውና ይህ ከአልሆነ በቀር ለሃይማኖታቸው ሌላ ምክንያት የላቸውም፡፡

ስአይአውቁትና ስአይመረምሩትም በእርሱ አመኑ፡፡ ሁልላቸውም እውነት ነው እየኣሉ ስለ እየሃይማኖታቸው ይጋደልኣልሉ፡፡ ነገር ግን ሁላቸው የሰዎች ሃይማኖቶች እርስ በእርሳቸው ይከራከራሉ እውነተኞች ሊሆኑ አይቻልም፡፡ ሐሰት ብዙ ሲሆን እውነትን ብቻዋ አንዲት ናትና ሁላቸው ግን ሐሰተኞች ሊሆኑ ይህ ይቻልኣል" በማለት በሰው ካተረፈነው እምነትና ሀይማኖት ልባችንን አንስተን የጥበብና የእውነት ሁሉ መገኛ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር እንድንመለከት ይጠይቀናል፡፡

እንግዲህ ወልደ ህይወት ይኽ አስተሳሰቡ ከመነሻቸው የሀይማኖተኞችን ቁጣ እንደሚያስከትል ያወቀ ይመስላል፡፡ ይሁንና ድፍረትን ለራሱና ለተከታዮቹ እንዲህ ይለግሳል፡- "ወዳጄ ሆይ ዓዋቂ አድርጎ ወደ ፈጠረህ ፍፁም ህላዌ ህሊናህን አንሳ፡፡ በልቦናህም ዓይን ወደ እርሱ ተመልከት፡፡ ፈጣሪህ ወደ የአሚኣሳይህ የብርሀን አእምሮ አስተውል ፤ የእሚሰድብህን ቃላቸውን አትስማ ፤ እነርሳቸውም ፈጣሪን አልዓወቁትምና በእነ እርሳቸውም ዘንድ ጥበብ የለም፡፡"

ወልደ ህይወት ከቀደሙት አስተሳሰብና እምነት ማፈንገጥ ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት የምንማርና የምንስማውም ቢሆን መርምረን መቀበል እንዳለብን ሲያስሰብን እንዲህ ይላል ፡- " አንተ ግን የአስተማሩህን ሁሉን ራስህ ሳትመረምረውና እውነትም ከሐሰት ስአትለይ በቀር ሰዎች የአስተማሩህን ምንም አትመን፡፡ ሰዎች ሊዋሹ ይችልኣልሉና ፤ እውነት ወይም ሐሰት ቢአስተምሩህም አትዓውቅም፡፡ እንዲሁም ሰአትመረምራቸውና እውነት ሁነው ሰአትኣገኘኣቸው ፤ በመፅሐፍት የተፃፈውን አትመን፡፡ መፃሕፍትን ከመረመርሃቸው እግዚአብሔር እወነት እንድንፈልግበት ከሰጠነ ከልቦናችን ጋር የእምአስይማማ ከፉ ጥበብ ተኣገኝባቸውአለህ፡፡"

ወልደ ህይወት የደረሰበትን እውነት ከመንገሩ በፊት ይኽን ያህል ማስጠንቀቁ ያለምክንያት የሆነ ድካም አይመስለንም፡፡ ብዙዎቹ ዕውቀትን ሳይመረምሩ በሰሙት ነገር ብቻ ከመወሰዳቸው የተነሳ በስንፍና ጨለማ ሲዳክሩ ተመለከትሁ በማለቱ እንጂ፡፡ እናም እውነትና ሐሰትን ለይቶ ለማሳወቅና የእግዚአብሔርን ስራ ለማመን አስቀድሞ እሱ በሰጠህ ህሊና ትመረምር ዘንድ የግድ ይሆናል፡፡ "መመርመር ወደ ጥበብ የምንገባበት በር ነው" የሚለን ወልደ ህይወት "እንግዲያስ ሰዎች የእሚአስተምሩንና በመፃህፍትም የተፃፈውን ሁሉ ልንመረምረው ይገባል" በማለት እሱ ህሊናዊ ምርመራ ደረስኩበት ወደሚለው የመደመሪያው ርዕስ ይዞን ይገባል፡፡ ወልደ ህይወት አስቀድሞ የሚያነሳልን "የፍጥረት ምርመራ" በማለት ያስቀመጠልንን ሐሳብ በመፈተሽ ይሆናልና ወደዚያው እንዝለቅ፡፡

ለወልደ ህይወት የሀይማኖት ፤ ጥበብና የእውነት መሰረት እግዚአብሔር ነው፡፡ ሁሉ በእሱ እንዳለና እንደሚኖር በቅድሚያ መሰረት መስያዝ ተገቢ መሆኑን አስቀምጦ በእሱም ማመን <መምህራን ሰዎችና የሁሉ አገር መፃህፍት> እንደሚስማሙ ልናውቅ ይገባል ይለናል፡፡ እኛም በእሱ እናምን ዘንድ የሚያስገድደን አንድ እውነት ቢኖር ዛሬ የአለን ትናንት ያልነበረንና ነገ የምንጠፋ ፍጡራን መሆናችንን ከመረዳት ላይ ሲሆን ይኸን እውነት ከተገነዘብን አለፈጣሪ ፍጡር መሆን እንደማይቻል ማሰብ አያቅተንም ባይ ነው፡፡

እንግዲህ ፍጥረት ሁሉ ከአንድ ፈጣሪ የወጣ መሆኑን መቀበል ከቻልን ሁሉን በትልቅ ጥበብ በፈጠረ በእሱ ዘንድ ስህተት አለመኖሩንም ማወቅ ሌላው ጥበብ መሆኑን ይነግረናል፡፡ ሁሉን በተወሰነለትና በሚገዛበት መንገድ ፈጥሮ እንደመራው የማይረዱ ሰዎች አሉ ፡- " ሁሉ ጊዜ ይህና ይህ መልካም ነው ፤ ይህ ግን በአይፈጠር በተሻለ የሚሉ ዕብዶችን አትስማቸው" በማለት ስለ እነሱም ከአስጠነቀቀን በኋላ ፡-"እግዚአብሔር የሰራው ሁሉ በሰራው መንገድ እጅግ መልካም ነው" በማለት ለእኛ እይታ የማይጠይቅም መስሎ የሚታየን የፍጥረት ክፍል ለሌላዕ በጎና የሚጠቅም መሆኑን እንድንረዳ ይመክረናል፡፡

በወልደ ህይወት አስተሳሰብ ፈጣሪ በምድር ላይ የፈጠረው ነገር ሁሉ ለሰው ጥቅም የተፈጠረ ነው፡፡ ለእኛ ጥፉዎች የሚመስሉን ሁሉ ከእኛ በኋላ ጥቅማቸው እንደተገኘ የሚነግረን ወልደ ህይወት ፡-" እንዲህ ሁሉ ለሰው ጥቅም ተፈጠረ፡፡ ወይም በይህ ዓለም ሃዳሪ ለሆነው ከፍጥረት ሁሉ የእሚልቅ ለሰው ማገልገያው ሊሆን ተፈጠረ፡፡ በይህ ዓለም ከአልለው ፍጥረት ሁሉ ሰው ከፍ የአለ ነውና ፤ በልቦናውም ወደ ፈጣሪው ምሳሌ ይበርባል፡፡ በይህ ዓለም ሁሉ የአለውም ለሰው ማደሪያና ማሳመሪው ምሳሌ ይቀርባል፡፡ በይህ ዓለም ሁሉ የአለውም ለሰው ማደሪያና ማሳመሪያ እንዲሆን ተፈጠረ" በማለት የሰው ልጅ ከፍጥረት ሁሉ የላቀ ፍጡርና የፍጥረት ገዢ ተደርጎ በእግዚአብሔር መሰየሙን ቀዳሚው ዕውቀት አድርጎ ያስቀምጣል፡፡

ምንም እንኳን ሰው የፍጥረት ሁሉ ገዢና አዋቂ ቢሆንም ሁሉን የሚያስብና የሚያውቀው በነፍሱ ጥልቀት እንጂ በስጋዊ ባህሪዩ አለመሆን ወልደ ህይወት ያስቀምጣል፡፡ የሰው ልጅ ስጋዊ ባህርዩ መሬት ነውና ተፍሱ ከእርሱ በወጣች ጊዜ "እንደ ደረቅ ጭላንፎ ይወድቃል" ይለናል፡፡ "መንፈሳዊትና ተነጋሪት ነፍስ" የሚላት ወልደ ህይወት በስጋችን ውስጥ ተመሽጋ ሁሉን እንድናውቅና እንድናስብ ብታደርገንም ስለምንፈሳዊያውን ፍጥረቶች ግን ለማወቅ አታስችለንም በማለት እንደሚከተለው ያስቀምጣል ፡- "ስለ መንፈሳዊያን ፍጥረትቶች ግን ከሰው ነፍስ የእሚልቁ ሌሎች መናፍስት እንደ አልሉ እጠረጥርአለ፡፡ እነ እርሳቸውም መላዕክትና አጋንንት ናቸው፡፡

ሰዎች ሁላቸው መኖራቸውን አምነዋልና ፤ በእግዚአብሔር ፍጥረታትም መኖራቸው ያምራል፡ ፡ ነገር ግን ለእኛ ስለ እምአይታዩን በይህ እምነት ላይ ልቦናችን ዝም ይላል፡፡እርግጠኛ ንግግርአቸው ልንአውቀው አንችልምና ስለ እነ እርሳቸው ልቦናችን ምንም አይኣረጋግጥልንም፡፡ ነገር ግን ለእኛ እርግጠኛ ከሰው ነፍስ የእሚአንሱ እንደ አልሉ እነርሳቸውም የእንስሳና አራዊት ነፍሳት ናቸው፡፡"

እዘህ ላይ ወልደ ህይወት እንደ መምህሩ ዘርአያዕቆብ ከዘመኑ የዘለማድ አስተሳሰብ አፈንጋጭ ሀሳቡን ቀስ ብሎ መሰረት ሲያበጅለት እናያለን፡፡ መላዕክትና አጋንንት በእግዚአብሔር ዘንድ ሊኖሩ ይችላሉ ፤ ነገር ግን እኛ ባለማየታችን ከፈጠረን ፈጣሪ በቀር ስለ እነሱ መኖር መናገር አንችልም ባይ ነው፡፡ ስለመኖራቸው ማረጋገጥ የማንችለውን ነገር እንደአሉ መቀበል ደግሞ ስንፍና መሆኑን ወልደ ህይወት አስቀምጦ እንስሳና አራዊትም ቢሆን በሰው ቋንቋ የሚነጋገሩ አይደሉምና "በህሊናቸው ስፋት የፈጠራቸው እንደአለና እንደሌለ የሚያውቁ አይመስሉኝም" በማለት የእነሱም ነፍስ ከሰውእንደሚለይ አስገንዝቦ የሰው ልጅ ከፍጥረት ሁሉ ታላቅ የመሆኑን እውነት አስቀድመን እንድንይዝ በማስገንዘብ ሐሳቡን መተንተን ይቀጥላል፡፡

የእንስሳትና የአራዊት ነፍስ ከሰው ሁሉ እንደምትለይ ወልደ ህይወት ሲነገረን የእሱ ህይወት ደግሞ "በአንድ ቦታ ተተክለው ተወልደው አድገው የእሚሞቱ እንጂ የእምአይንቀሳቀሱ ከአትክልትና ከአዝርዕት ህይወት የእንስሳና የአራዊት ተፈጥሮነት ከፍ እንደሚል እንዲሁ የሰው ነፍስ ከእንስሳ ነፍስ ከፍ ይላል" በማለት በተፈጥሮ ደረጃ የሰው ልጅ ከሁሉ የላቀ ስፍራ እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የሰው ነፍስ ወደ ፈጣሪ በሁሉ ነገሯ በእጅጉ የቀረበች በመሆኗ "የመጀመሪያውን ማዕረግ" እንደተሾመች እንድንአዳና በዚህ ማዕረጓ ምክንያት ሟች እንዳልሆነች እንረዳ ይለናል፡፡

የሰው ነፍስ የማትሞት ስትሆን የእንስሳትና የአራዊት ነፍስ ግን ይሙት ወይም አይሙት አላውቅም የሚለው ወልደ ህይወት ይኸም በመሆኑ "የነፍስ ዕውቀትዋ ህላዌዋ ነው ፤ የነፍስ ዕውቀትም ከእግዚአብሔር ከፈጣሪ የወጣ የብርሀን ጮራ ነው ፤ ወደ እርሱ ተመልሶ ይገባል እንጂ አይጠፋም ፤ ከቶም ሊጠፉ አይችልም" በማለት የሰውን ነፍስ ዘላለማዊነት አለጥርጣሬ እናምን ዘንድ እንደሚገባ ይመክራል፡፡

"ስለ ይህም የዘለዓለምን ህይወት የነባቢት ነፍስ አስፈላጊዋ ነው፡፡ አለ ይህ ግን የሰው ህላዌ ሁሉ ምትሀትና ከንቱ ይሆንኣል፡፡ እግዚአብሔርም በሰው ፍጥረት ጠቢብ ሳይሆንነ አልላጋጭ በሆነ" በማለት ወልደ ህይወት የሰውን ነፍስ ዘላለማዊነት ከፈጣሪው ማንነት ጋርያቆራኝውና ይህንንም ማሰቡና ማመኑ በራሱ ምድራዊ ኑሮአችንን እንደሚያጣፍጥ እንገንዘብ ይለናል፡፡ "እንግዲህ ነፍሳችን ሙዋች እንደ አይደለች አለጥርጣሬ ልናምን ይገባንኣል፡፡

ከፈጣሪዋ ጭን የበረረች ሁና እንደወጣች እንዳይሁእይህ ኑሮ በጎ ወደ እርሱ ትገባለች፡፡ እንደይሁ እንደሆነም ልቦናችን የአርረጋግጥልናል፡፡ ይህም ትምህርት ሐሳባችነን ያስደስታል ፤ በእውነትነና ለመልካም ስራ ሁሉ መሰረት ይሆነንኣል" በማለት ወልደ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## Invitation to Bid

Place and Date: *Dire Dawa, January, 2024*

Procurement Reference Number: *DDA/K02AO/PC-001/2016*

1. The ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** having legal address at:

| | |
|---|---|
| Street Address: | Seyido taxi station street |
| Town/City: | Dire Dawa |

2. The ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** now invites sealed bids from eligible and qualified bidders for: ***Construction of Ditch Work (Location: Bargele, Kebele 02)***.
3. Intended Completion Date for the whole of the Works shall be ***150 calendar days***.
4. Bidding will be conducted through **National Competitive Bidding** procedure contained in public proclamation of FDRE and is open to all Eligible bidders.
5. Interested eligible bidders may obtain further information from ***Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office*** and inspect the bidding documents at the address given below from 7:30AM – 12:00 PM & 2:00 – 5:30 PM working hours.
6. Qualifications requirements include: Contractors of category ***GC/BC-7 & above*** with license valid for the year ***2016E.C. Work Experience is Required***
7. A complete set of Bidding Documents in English may be purchased by interested bidders on the submission of a written Application to the address below and upon payment of a non-refundable fee of ***ETB 500*** in ***Cash***.
8. Bidders shall submit their Bids in **two envelopes**, the first envelop labeled as "Technical Proposal and Bid Security" and the second envelope "Financial Proposal", separate sealed and the two envelopes sealed in on other outer envelope.
9. Evaluation is to be carried out in two stages, Technical Proposal first and Financial Proposal of qualified Bidders next.
10. Bids must be delivered to the address below at or *before* ***9:00 AM morning time*** on the $22^{nd}$ Date from the Date of Announcement. Late bids will be rejected.
11. Bids Will Be Opened In The Presence Of Bidder's Representatives Who Choose To Attend at The Same Date of Submission at ***9:30 AM morning time***
12. All bids must be accompanied by a Bid Security of ***ETB 100,000.00 (One Hundred Thousand Ethiopian Birr) in the form of Cash, an Unconditional Bank Guarantee, or CPO***. The Bid Security shall be valid for 28 days beyond the validity of the Bid.
13. The public body reserves the right to reject any bid and to annul the bidding process and reject all bids at any time prior to contract award, without thereby incurring any liability to Bidders.
14. The address referred to above is:

| | |
|---|---|
| Public Body: | Dire Dawa Administration Kebele 02 Administration Office |
| Street Address: | Seyido taxi station street |
| Town/City: | Dire Dawa |

## የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 005/2016

ገቢዎች ሚኒስቴር ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ከምደር ክፍሎች ጀምሮ ያለውን ህንፃ ለመከራየት ህጋዊና ብቃት ያላቸውን የሐገር ውስጥ ተጫራቾችን በግልፅ ጨረታ ማወዳደር ይፈልጋል፡፡

እያንዳንዱ የጨረታ ተካፋይ የሚከተሉትን ጨረታ መመሪያ ነጥቦች በግልጽ በመረዳት በጨረታ ሰነዶች ላይ እንዲሟላ ማድረግ አለበት፡፡

1. የጨረታው ሰነዱን ማስተወቂያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በቅ/ጽ/ቤቱ በ3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 310 ገንዘብ ቤት 500.00 (አምስት መቶ ብር) መግዛት ይችላሉ፡፡
2. ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ህንፃ ኪራይ አገልግሎት ግዥ ለቢሮ አገልግሎት በሚውል ደረጃ የተሰራና ምቹ ህንፃ መሆን ይጠበቅበታል፤
3. ተጫራቾች በዘርፉ የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸውና ለዘመኑ ስለመታደሱ የተረጋገጠ ማስረጃ፣ VAT (የተጨማሪ እሴት ታክስ)፣ TIN (ግብር ከፋይ ምዝገባ ም/ወረቀት) ተመዝጋቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ከላይ በተራ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሱት ማስረጃዎች አሟልቶ ያላቀረበ ተጫራች ከውድድር ውጪ የሚደረግ መሆኑት ተጫራቾች ከወዲሁ ሊያውቁት ይገባል፤
5. ተጫራቾች የሚወዳደሩበት ህንፃ መ/ቤቱ በሚመድበው ባለሙያ ይገመግማል፡፡
6. ተጫራቾች የአገልግሎት የዋጋ ዝርዝር እና ሌሎች በተጫራቾች የሚሞሉ ቅፆች ላይ ሞልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤
7. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ ብር) በባንክ በተመሰከረ ሲፒኦ አልያም ደግሞ በጥሬ ገንዘብ፣ በሁኔታ ላይ ያልተመሠረት የባንክ ዋስትና ከላይ ከተጠቀሱት አንዱ ዝርዝር ውስጥ በተጫራቹ ምርጫ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
8. ጨረታው ጥር 29/2016 ዓ.ም እስከ የካቲት 13/2016 ዓ.ም ድረስ ቆይቶ በማግስቱ ሐሙስ የካቲት 14 ቀን 2016 ዓ.ም ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ተዘግቶ3፡30 ይከፈታል፡፡
9. አሸናፊው ድርጅት ከመ/ቤቱ ጋር ውል ለመዋዋል ፈቃደኛ መሆን ይኖርበታል፡፡
10. ቅ/ጽ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
11. ተጫራቹ የሚሞላው ሰነድ በጥንቃቄ እንዲሞላና ስርዝ ድልዝ የሌለው መሆን ያለበት ሲሆን የጨረታ ሰነዱ በእርሳስ መሞላት የለበትም፡፡

ለበለጠ መረጃ

- በስልክ ቁጥር 025-411-65 51 ድሬዳዋ ገቢዎች ሚኒስቴር ግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ቡድን በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

## በድጋሚ የወጣ የግዢ ጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ለ2016 ዓ.ም የአይ.ሲ.ቲ የመሠረተ ልማት ዕቃዎችን በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህበ ጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ሁሉ ከዚህ በታች የተመለከቱትን

መስፈርቶች በሚሟላት መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. ተጫራቾች የቫት ተመዝጋቢ፣ በሥራው መስክ ህጋዊና የታደሠ የንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ለእያንዳዱ ሰነድ 5000.00 (አምስት ሺህ ብር) በባንክ በተመሠከረ ቼክ (CPO) ከጨረታ ሠነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፣
3. ተጫራቾች የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የግዢ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ ዳይሬክቶሬት መግዛት ይችላሉ፡፡
4. በጨረታው አሸናፊ የሚሆኑ ተጪራቾች በጨረታ ሠነድ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎች (ለተጫረቱበት) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከእያንዳንዱ ዕቃ ናሙና ወይም Sample ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች ላሸነፉባቸው ዕቃዎች የጠቅላላ ዋጋ 10% በውል ማስከበሪያነት ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ዋጋቸውን በገዙት የጨረታ ሠነድ ላይ ባለው ዝርዝር ሞልተው ኦርጅናልና ኮፒ በማድረግ ለዚሁ በተዘጋጀው ድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የጨረታ ሳጥን በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀንጀምሮ 15 ተከታታይ ቀናት ማስገባት ይችላሉ፡፡
7. የጨረታው ሳጥን የሚዘጋው በ16ኛ ቀን በዕለቱ በ 3፡30 ሠዓት ሆኖ ጨረታው የሚከፈተው በዕለቱ 4፡00 ሠዓት ተጪራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የግዢ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደርዳ ይሬክቶሬት ይከፈታል፡፡
8. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በ10 ቀናት ውስጥ በራሳቸው ትራንስፖርት በማጓጓዝ ቢሮው ግቢ ድረስ አምጥተው ያስረክባሉ፡፡
9. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብት አለው፡፡

- ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0251310011ወይም 0912994637 በመደወል ማብራሪያ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የድሬዳዋ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ

## Invitation to Bid Notice (LCB)

Proc. Ref/No: DDA/HB/PC-010/2016

1, To: ALL ELECTRONICS AND MOTOR BIKE SUPPLAYERS WITH LICENSE VALID FOR THE YEAR 2016

2, the D.D Administration Health Bureau has fund with procurement entity budget to be used for the procurement of Electronics & Motor Bike for Health Bureau

3, all eligible bidders should present from the mandated public body:

- Renewed trade license for the year
- Supplier certificate in Dire Dawa Administration
- Tax clearance and VAT registration certificate

4, A complete set of bidding document may be purchased by any interested eligible bidder on the submission of a written application to the D.D Administration Health Bureau Room No __ up to payment of 200(two hundred BIRR ONLY)

5, Bidding will be, conducted in accordance with open national tendering procedures contained in the public procurement proclamation of the Federal Gov't of Ethiopia and is open to all bidders from eligible source countries.

6, interested eligible bidders may obtain further information from D.D Administration Health Bureau and inspect the bidding document at the address given below from 7:30- 12:00Am & 2:00-5:30 pm working hours.

7, Bids must be delivered to the address below at or before 9: 00A.M on the 15th Date from the date of Announcement. Bids shall be valid for a period of 60 days after bid opening and all bids must be accompanied by a bid security 5,000(Five thousand birr) in the form of cash, a certified check or payable order, bank draft, letter of credit, or an unconditional bank guarantee. The bid security shall be valid for 28 days beyond the validity of the bid. Late bids shall be rejected.

8, Bids will be opened in the presence of bidders representatives who choose to attend at the same place & Date at 9:30AM at the office of D.D Administration Health Bureau

9, The supply and commissioning shall be complete within a maximum 20 calendar days from the commencement of the work.

10, The Employer Reserves The Right to Reject Any or All Bids

Address: D.D Administration Health Bureau

Telephone No. 025-1-11-23-30 e-mail address ddhealth@ethionet.et

Post No. 1377

# ኢጋድ ከሰሞኑ.... .

በኤደን ሳሙኤል

የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በይነ መንግሥታት የልማት አጋርነት ድርጅት ኢጋድ በ1988 ዓ.ም ነበር የተመሰረተው፤ ሲመሰረትም ከዚህ በፊት የበይነ መንግሥታት የድርቅ እና የበረሃማነት አጋርነት ባለስልጣን ተብሎ ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ በአፍሪካ ቀንድ ከድርቅ እና ከበረሃማነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የተቋቋመውን ለመተካት የተፈጠረ ድርጅት ነው።

ኢጋድ በአዲስ ስም፣ ድርጅታዊ መዋቅር እና በአባላቱ መካከል ሰፊ ትብብር የማድረግ የላቀ ስሜት በመያዝ ህልውናውን አስቀጥሏል።

በ1976 ዓ.ም ኢጋድ ጅቡቲ ላይ የተመሰረተው የበይነ መንግሥታት የድርቅ እና በረሃማነት አጋርነት ባለስልጣን ተብሎ በሚኒስትር ደረጃ በተደረገ ስብሰባ ላይ ነበር። ስድስቱ መስራች ሀገራትም ጅቡቲ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ እና ኡጋንዳ ናቸው፡፡

ሀገራቱንም ቀጣናው በ1970ዎቹ መጨረሻ እና በ1980ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በተከሰቱ አሰቃቂ የድርቅ አደጋዎች መመታት ወደ አንድነት አምጥቷቸዋል።

ኢጋድ መጀመሪያ ላይ እንደ አንድ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መንገድ፣ የዓለም አቀፉን ማሕበረሰብ እና አባላቱን ለቀጠናው ሰብዓዊ አደጋዎች በማንቃት እና እንደ አንድ የማስተባበሪያ አካል ችግሮችን ለመቋቋም ሀብትን የሚያሰባስብ ተደርጎ ይታይ ነበር።

የቀድሞው የኬንያ ፕሬዚደንት ሚይ ኪባኪ የመሩት የሱዳን የሰላም ድርድር ሂደት ነበር ኢጋድን ወደ መድረክ ያወጣው፤ ሂደቱም በ1985 ዓ.ም የተቀላቀለችውን ኤርትራን ጨምሮ፣ አባል ሀገራቱን ድርጅቱን የተሻለ አደራጅቶ ሰፊ ቀጣናዊ ጉዳዮችን እንዲያስተናግዱ መርቷቸዋል።

ድርጅቱን የማጠናከር እና የማደራጀት ሂደቱ የተጠናቀቀው በ1988 ዓ.ም ነበር። ከዚያም የምግብ ዋስትና እና አካባቢያዊ ጥበቃ፣ ግጭት መከላከልን፣ መቀነስን እና መፍታትን ያካተተ ፖለቲካዊ እና ኢሰብዓዊ ጉዳዮች እና ቀጣናዊ ኢኮኖሚያዊ ትብብር የኢጋድ ሦስት የትኩረት ዘርፎች በመሆን ተለዩ። የኢጋድ ሴክሬታሪያት የድርጅቱ አስፈፃሚ አካል ነው። መቀመጫውን ጅቡቲ አደረገ።

አስፈፃሚ ሊቀመንበር በመሆን ኤርትራዊው ዶ/ር ተከስተ ገብራይ እንዲመሩት ተደረገ፤ ሌሎች ባለሙያዎች




ከንኡስ ቀጣናው እንዲመለመሉ ተደርጎ ሥራውን በአዲስ እንደጀመረ ከድርጅቱ ድረ ገጽ ያገኘነው መረጃ ታሪኩን ያስረዳል። አለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች በተቋቋመው ጥምር የኢጋድ አጋሮች ፎረም አማካይነት ለቀጣናዊ ጉዳዮች መፍትሔ ለመዘየድ፣ ከኢጋድ እና አባል ሀገራት ጋር በቀጥታ የሚሳተፉበት አሠራር ተዘርግቷል።

በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያዊው ዶ/ር ወርቅነህ ገበየው እየመሩት ሲሆን የአባል ሀገራቱ ቁጥር ስምንት ደርሷል። በአጠቃላይ በቀጣናዊ ትስስር ረገድ ኢጋድ ከአቅሙ ከግማሽ በታች ነው ያሳካው። ለዚህ በማሳያነት ደግሞ አባል ሀገራ የሚገኙበት ቀጣናው ከግጭት ተላቆየማያውቅ መሆኑ ነው በዋናነት የሚነሳው፤ ኢጋድ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበው በሰዎች ነፃ እንቅስቃሴ ነው፡፡

ለዚህም አብዛኞቹ አባል ሀገራት በአህጉሪቱ ነፃ እንቅስቃሴ እንዲረጋገጥ በትኩረት በመሥራታቸው ነው። ይሁን እንጂ በጣም መሻሻል ያለበት የማምረት ዘርፉ ነው። ኡጋንዳ በተቀኛጀ ምርት እና በተቀናጀ ንግድ ዘርፍ ኢጋድን ትመራለች። መካከለኛ ምርቶችን በቀጣናው ውስጥ በመላክ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግባለች። በተጨማሪም በቀጠናው የተሻለ የንግድ ድርሻ የያዘች እና በውጭ እቃዎች የሁለተኛነት ድርሻ አላት።

ኢትዮጵያ በማክሮኢኮኖሚያዊ ትስስር በጥሩ ውጤት ትመራለች። ኬንያ በተቀናጀ መሰረተ ልማት ቀዳሚ ናት። ጅቡቲ እና ሶማሊያ በነፃ የሰዎች እንቅስቃሴ ቀዳሚ ፈፃሚዎች መሆናቸውን የአፍሪካ ቀጣናዊ ትብብር ኢንዴክስ ድረ ገፅ ያሳያል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢጋድ ካለፈው የፈረንጆች 2013 ዓመት ወዲህ በርካታ ተግዳሮቶችን እያስተናገደ ይገኛል። ቀጣናዊ አለመረጋጋት፣ የአባላት ትስስር መላላት እና ደካማ የንግድ ትስስር ተጠቃሽ ናቸው።

በሱዳን ተፋላሚዎች መካከል ላለፉት ዘጠኝ ወራት እየተካሄደ የሚገኘው ጦርነት እስካሁን እልባት ያላገኘበት ሁኔታ በኢጋድ ላይ የተጫነ ሸክም ሆኗል። ኢጋድ በ1997ዓ.ም የሱዳንን የሰላም ድርድር ሂደት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ያደረገ ሲሆን በውጤቱም 22 ዓመታትን የፈጀውን ግጭት በመፍታት ረገድ የኢጋድ ተሳትፎ ከፍተኛ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሶማሊያ ጦርነት ወቅት የሽግግር መንግሥት ምስረታውን በበላይነት ተቆጣጥሮ ዳር አድርሷል።

በተመሳሳይ የኢጋድ ወታደራዊ ኃይል በአሁኑ ወቅት የሶማሊያን አለመረጋጋት እልባት በመስጠት ላይ ላለው የአፍሪካ ሕብረት ስምሪት ቀዳሚ መንገድ ከፋች የነበረበትን ስኬት ቢቢሲ ያወሳል። ሱዳን በቅርቡ በሌላ ጦርነት ውስጥ ከገባች ወራት አስቆጥራለች፤ ሁለቱ ተፋላሚ ወገኖች እንዲስማሙ ለማድረግ በኡጋንዳ ካምፓላ የኢጋድ አባል ሀገራት መሪዎች ለስብሰባ ተገናኝተው መክረዋል።

በጉባኤው ኢጋድ ሁለቱም ተፋላሚ ወገኖች እንዲገኙ ጋብዞ የነበረ ቢሆንም የሱዳን ወታደራዊ መንግሥት መሪ አብደል ፋታህ አል ቡርሃን፣ ተፋላሚያቸው የሱዳን ፈጥኖ ደራሽ ኃይል መሪው ጄኔራል መሃመድ ሃምዳን ዳጋሎ መጋበዛቸውን ሲያውቁ በስብሰባው እንደማይገኙ አስቀድመው ማሳወቃቸው ተዘግቧል።

ጄኔራል አብደል ፋታህ አል ቡርኃን ኢጋድ ዳጋሎን መጋበዙ የሱዳንን ሉዓላዊነት እንዳለማክበር አድርገው ቆጥረውታል፤ ቅሬታቸውን ከመግለፃቸው በተጨማሪም ሰሞኑን ለጊዜው ከኢጋድ አባልነቷ ሱዳን እራሷን እንዳገለለች በውጭ ጉዳይ ሚንስትራቸው በኩል አሳውቀዋል፡፡ በስብሰባውም አልተሳተፈችም፡፡

ይም የሰላም ሂደቱን እንደሚያወሳስበው እየተነገረ ነው። የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢጋድ ጋር ያለውን ግንኙነት መቋረጡን የሚነግር መግለጫ አውጥቷል።

ከሁለት ቀናት በኋላም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከዚያ ያለፈ ርቀት በመሄድ፣ ሱዳን በኢጋድ በመግለጫው የመጨረሻ ሀሳብ ምክንያት ከኢጋድ አባልነቷ መውጣቷን አስታውቋል። በቅርቡ በተካሄደው የኢጋድ ስብሰባም የአባል ሀገራቱ መሪዎች በዋናነት የሱዳንን የእርስ በርስ ጦርነት በተመለከተ እና በሰሜናዊው የሶማሊያ እና ኢትዮጵያ በወደብ ስምምነቱ ላይ በተነሳው ውጥረት ላይ መወያየታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል፤ በተመሳሳይ ኢጋድ በሱዳን አፋጣኝ እና ያለ ቅድመ ሁኔታ የተኩስ አቁም እንዲደረግ ጥሪ አቅርቧል።

አጃንስ ፍራንስ ፕረስ (AFP) እንደዘገበው በስብሰባው የመጨረሻ የመዝጊያ መግለጫው ላይ ኢጋድ በተጨማሪ በጄኔራል አብደል ፋታህ አል ቡርሃን የሚመራው የሱዳን መከላከያ እና በሃምዳን ዳጋሎ የሚመራው ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ በሁለት ሳምንት ውስጥ ፊትለፊት ለንግግር መቀመጥ እንዳለባቸው አሳስቧል።

የሱዳናውያንን ሕይወት እየቀጠፈ፣ ሱዳንንም ወደ ፍርስራሽነት እየቀየረ ያለው የእርስ በእርስ ጦርነት ፈጣን እና ያለ ቅድመ ሁኔታ የተኩስ ማቆም እንዲደረግ ኢጋድ ያቀረበውን ጥሪ ያወሳው የአልጀዚራ ዘገባ በተጨማሪ ድርጅቱ ሁሉን አቀፍ የሰላም ውይይት ሂደት እንዲቀጥል ለማድረግ ዝግጁነቱን መግለፁን ጠቅሷል።

የሱዳን ውጭ ጉዳይ ሚንስቴርም የስብሰባውን የአቋም መግለጫ የሱዳንን ሉአላዊነት የጣሰ እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ (በሱዳም ወታደራዊ መንግስት አጠራር - አማፂ ሚሊሺያ) ጥቃት ሰለባ የሆኑ ዜጎችን ስሜት ማቁሰል እንደሆነ በመግለጫው ኮንኗል።

በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ቀንድ ያለው ሁኔታ ከፍተኛ ምስቅልቅል ውስጥ እየገባ ሲሆን ይህም ኢጋድን አጣብቂኝ ውስጥ አስገብቶታል፤፤ ኢጋድ አባላቱ እርስ በርስ እያሳዩት የመጡት አለመግባባት እና ችግሮችን ተቀራርቦ ለመፍታት ፍላጎት አለማሳየት የድርጅቱን የወደፊት ሕልውና አደጋ ላይ ጥሎታል፡፡

# የኢትዮጵያና . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ግንኙነት መምህር ረዳት ፕሮፌሰር ሚፍታህ መሐመድ በበኩላቸው፤ ሀገራችን በሰጥቶ መቀበል መርህ የአመታት ጥያቄዋን ለመመለስ እያከናወነችው ያለው ተግባር አበረታች ነው ብለዋል።

የተጀመረው ጥረት እንዲሳካ የምሁራን ሚና ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት በማከል። ረዳት ፕሮፌሰር ሚፍታህ እንደገለፁት፤ የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ እንዲሳካ ምሁራንን በቅርበት በማሳተፍ የተሻለ ስራ መስራት እንደሚገባ ተናግረዋል። ይህም የትውልድን ፋላጎትና ህልውና ለማረጋገጥ ያስችላል ብለዋል።

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ተማም አወል የመግባቢያ ስምምነቱ የቀጣናውን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚያሳድግ መሆኑን ተናግረዋል። ዶክተር ተማም፤ ሌሎቹ የቀንዱ ሀገራት ወደ ስምምነት ማዕቀፉ በመግባት የተሻለ ብልፅግና፣ ዘላቂ ሰላምና ልማትን ለማረጋገጥ መትጋት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

መረጃው የኢዜአ ነው፡፡

## የአካባቢ ጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ውሃና ፍሣሽ ባለሥልጣን ሰ2016 በጀት ዓመት የምንጠቀምበት ከ10-12 ቶን ክብደት ያለው ፖንፕ ከውሃ ጉርጓድ የሚያወጣ የክሬን አገልግሎት በአካባቢ ጨረታ አወዳድሮ ለአንድ አመት ውል ፈጽሞ ለማሰራት ይፈልጋል፡፡ እንዲሁም የአገልግሎቱን ጥራት እና ቀልጣፋ አገልግሎት ታይቶ ለተጨማሪ የአንድ አመት የሚራዘም ይሆናል፡፡

ስለዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መሰፈርቶች የሚያሟሉ ተወዳዳሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

- ማንኛውም ተጫራች በዘርፉ በዕቃና አገለግሎት አቅራቢነት በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመዝገቡን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣ በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት መወዳደሪያ ኤንቨሎፑ ውስጥ በማድረግ እስከ ጨረታው መዝጊያ ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- የጨረታው ዶክመንት የማይመለስ ብር 300 /ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል ድሬዳዋ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ከግዥ ፋይናንስና ደጋፊ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 05 በጥሬ ገንዘብ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
- የጨረታ ሰነድ በውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ቢሮ ቁጥር 05 ከ1፡30 እስከ 11፡30 ሰዓት ዘወትር በሥራ ሰዓትና ቀን መግዛትና ማስገባት ይቻላል፡፡
- ጨረታው በማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15ኛው ቀን በ4፡00 ሰዓት የጨረታ ሳጥኑ ተዘግቶ በተመሳሳይ ቀን 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው ይከፈታል፡፡
- የጨረታው ዶክመንት በታሸገ ፖስታ የእያንዳንዱ ዋጋና ጠቅላላ ዋጋ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት በተጨማሪ በጨረታ ዶክመንቱ ውስጥ የተዘጋጁት ፎርማት ተሞልተውና ተፈርመው መቅረብ አለባቸው፡፡
- በዶክመንቱ ከተሰጠው ስፔስፊኬሽን ውጪ የሚቀርብ ተቀባይነት የለውም፡፡
- የጨረታው አሸናፊ ካሸነፈው ዋጋ 10% ውል ማስከበሪያ በተረጋገጠ የባንክ ዋስትና CPO ወይም በሁኔታ ያልተገደበ የባንክ ጋራንቲ ማሰያዝ መስጠት የሚችል፡፡
- በጨረታው ሂደት ጨረታውን ለማዛባት ለማጭበርበር የሞከረ ተጫራች ከጨረታው ውጭ እንደሚሆንና በመንግሥት ግዥ እንዳይሳተፍ ይደረጋል፡፡
- የጨረታ ሳጥኑ ከተዘጋ በኋላ የሚመጣ የጨረታ ዶክመንት ተቀባይነት የለውም፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

አድራሻ፡-ድሬዳዋ አስተዳደር ውሃና ፍሣሽ ባለሥልጣን ቀበሌ 03 ድሬዳዋ ስልክ ቁጥር 025 112 48 92 ፖ.ሣ.ቁ 446

## "የድሬዳዋ የሌሊት ታክሲ አሽከርካሪዎች ማህበር አባላት በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዬች ላይ በመሳተፍ እያከናወኑ ያሉትን በጎ ተግባራት አስተዳደሩ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል"

*ክቡር አቶ ሀርቢ ቡህ*

*የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የንግድ ኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ*

"በጎ ማድረግ ለራስ ነው"

ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ

የድሬዳዋ የሌሊት ታክሲ አሽከርካሪዎች ማህበር በዛሬው ዕለት ደም የመለገስ መርሀ ግብር አከናወኑ ።

ይህ የደም ልገሳ መርሀ ግብር የተከናወነው የማህበሩ አደራጅ የሆነው የትራፊክ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ም/ኮማንደር ይሄነው ሽፈራው የልደት ቀንን ምክንያት በማድረግ ነው ።

በመርሀ ግብሩ ላይ የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የንግድ ኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ ክቡር አቶ ሀርቢ ቡህ ፣ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ ፣ የድሬደዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ ኃላፊ ክቡር ም/ኮሚሽነር ማኡ ተሾመ ፣ በድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ የፈውስ ህክምና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ክቡር አቶ አብዶ ሙሜ በየ ደረጃ የሚገኙ የአስተዳደሩ እና የድሬዳዋ ፖሊስ ከፍተኛ አመራሮች ተገኝተዋል ።



የድሬዳዋ አስተዳደር የሌሊት ታክሲ አሽከርካሪዎች ማህበር ያካሄዱት ደም የመለገስ መርሀ ግብር ላይ በመገኘት መልዕክት ያስተላለፉት የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የንግድ ኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ ክቡር አቶ ሀርቢ ቡህ እንደተናገሩት የድሬዳዋ የሌሊት ታክሲ አሽከርካሪዎች ማህበር በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዬች ላይ በመሳተፍ እያከናወኑ ያሉት በጎ ተግባራት አስተዳደሩ ትልቅ ቦታ እንደሚሰጠው ጠቅሰው በዛሬው ዕለትም ደም ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች አለኝታነታቸውን ለማሳየት ላደረጉት ላቅ ያለ ተግባር ምስጋናቸውን አቅርበዋል ።

በጎ ማድረግ ለራስ ነው ያሉት የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ የድሬዳዋ የሌሊት ታክሲ አሽከርካሪዎች የድሬዳዋ ወጣት ሊገለፅበት የሚችለውን መንገድ በመያዝ የድሬዳዋ ወጣት በኢትዮጵያ ወጣቶች ውስጥ ጎልህ ስፍራ እንዲይዝ እና ምሳሌ እንዲሆን ለማስቻል በማህበራዊ ጉዳዮች እና በተለያዩ መስኮች እያደረጉ ያሉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

የሌሊት ታክሲ አሽከርካሪዎች ላደረጉት በጎ ተግባር ምስጋና ያቀረቡት ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ ይህ ተግባር በቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

በመርሀ ግብሩ ላይ በአጠቃላይ 180 ዩኒት ደም መሰብሰብ ተችሏል ።

## < <በሃገር አቀፍ ደረጃ እየተመዘገበ ያለውን አስገራሚ ለውጥ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስቀጠል ቅንጅታዊ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል> >

*ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ*

*የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ*

‹‹የገጠር ፖሊስ ጣቢያዎች እና የሚሊሻ አባላት ስራዎችን በቅንጅት መስራት ይገባቸዋል››

ክቡር አቶ አብደላ አሜ

የድሬዳዋ አስተዳደር ፍትህ ጸጥታ እና ህግ ጉዳዬች ም/ቢሮ ኃላፊ

የድሬዳዋ ሰላም እና ጸጥታ በዘላቂነት አስተማማኝ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል ቅንጅታዊ ስራዎች ሊሰሩ እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

በወቅታዊ ጉዳዬች ላይ በድሬዳዋ የሚገኙ ሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች እና የፌደራል ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ምስራቅ ምድብ አመራሮች ውይይት አካሄዱ፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ እንደገለጹት በሃገር አቀፍ ደረጃ እየተመዘገበ ያለውን አስገራሚ ለውጥ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስቀጠል ቅንጅታዊ ስራዎች ሊሰሩ እንደሚገባ ጠቅሰው ሀገራዊ ፤ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስጋቶችን በአግባቡ በመተንተን ለዛ



በቂ ምላሽ መስጠት የሚያስችል የፀጥታ ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

በድሬዳዋ ከተማ ያለውን ሰላም እና ጸጥታ ለማስቀጠል ቀጣይነት ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እንደሚገባ የገለጹት የድሬዳዋ አስተዳደር ፍትህ ጸጥታ እና ህግ ጉዳዬች ም/ቢሮ ኃላፊ ክቡር አቶ አብደላ አሜ የድሬዳዋ ፖሊስ ባሳለፍነው የጥምቀት በዓል አከበበር ላይ የታየው ቅንጅታዊ ስራ አበረታች መሆኑን ጠቅሰው ይሄው ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

የገጠር ፖሊስ ጣቢያዎች እና የሚሊሻ አባላት ስራዎችን በቅንጅት እየሰሩ መሆኑን የገለጹት ክቡር አቶ አብደላ አሜ ከህብረተሰቡ ጋር እጅ እና ጓንት ሆኖ በመስራት የሀገራችንን እድገት ማረጋገጥ እንደሚገባ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

በመድረኩ የድሬዳዋ ሰላም እና ጸጥታ በዘላቂነት አስተማማኝ ሆኖ እንዲቀጥል በሚያስችል መልኩ የተለያየ ጥያቄ ተነስቶ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ ውይይቱ ተጠናቋል፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ በድሬዳዋ የሚገኙ ሁሉም ፖሊስ ጣቢያዎች እና የፌደራል ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ምስራቅ ምድብ አመራሮች ተገኝተዋል፡፡

## ናይል ሚኒራል ወተር ኤንድ ቢቨሬጅ ድርጅት የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በጀመረው እራሱን በቴክኖሎጂ የማስታጠቅ ስራ የሚውል የዋጋ ግምታቸው ከአራት መቶ ሺ ብር በላይ የሆኑ ሁለት ዘመናዊ ኮምፒዩተሮች ድጋፍ አደረገ

ይሄው ድጋፍ ተቋሙ ለጀመረው ስራዎችን በቴክኖሎጂ የማከናወን ተግባር እጅግ ከፍተኛ የሆነ እገዛ እንደሚኖረው በርክክቡ ወቅት ተገልጻል፡፡

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ እያከናወነ ባለው ዘርፈ ብዙ ስራዎች መደነቃቸውን የገለጹት የናይል ሚኒራል ወተር ኤንድ ቢቨሬጅ ድርጅት ባለቤት አቶ ዚያድ መሃመድ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አሁን በያዘው የከተማውን ሰላም እና ጸጥታ የማረጋገጥ ስራ በቴክኖሎጂ ተደግፎ እና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል ድጋፉን ማድረግ መቻላቸውን ጠቅሰው ይሄው ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

ድጋፉን የተረከቡት በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የኮሚሽነር ስታፍ ዳሬክቶሬት ዳሬክተር ኮ/ር ዝናቧ በቀለ በበኩላቸው እንደገለጹት ለተደረገው ድጋፍ ለናይል ሚኒራል ወተር ኤንድ ቢቨሬጅ ምስጋናቸውን



ያቀረቡ ሲሆን የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በለውጥ ጎዳና ላይ መሆኑን የገለጹት ኮ/ር ዝናቧ በቀለ ተቋሙ እራሱን በቴክኖሎጂ ለማስታጠቅ እያደረገ ላለው ስራ የተደረገው ድጋፍ ከፍተኛ እገዛ እንዳለው ጠቅሰው የከተማችንን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ ከህብረተሰቡ ፤ከጸጥታ አካላት፤ ከባለሃብቱ ጋር በጋራ እያከናወኑ ያሉትን ስራዎች አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ጨምረው ተናግረዋል፡፡




በምርመራ ወቅት በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠ የምስክሮች ቃል በፍ/ቤት ያለው ተቀባይነት፤ ሕጉ፣ ትግበራው እና የሰበር ችሎት

አንድ ወንጀል ስለመፈጸሙ እና ድርጊቱን ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጣሪው ሰው የድርጊቱ ፈጻሚ ስለመሆኑ ፖሊስ ምርመራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ከሚያጣራባቸውና ከሚያረጋግጥባቸው የማስረጃ ዓይነቶች መካከል አንዱ የሰው ምስክሮች ናቸው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ የዚህ ጹሁፍ ዓላማ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 145ን ህጉን ፤በፍ/ቤት ትግበራ ያለውን የህጉን ትርጉም እና የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም አቋምን ከተከሳሽ መብት አኳያ በማመዛዘን ያስዳስሳል፡፡

የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 145

በፖሊስ ምርመራ የተሰጠ ቃል በማስረጃነት ሊቀርብ ስለመቻሉ

(1) ዐቃቤ-ህጉ ወይም ተከሳሹ ሲያመለክት በፖሊስ ምርመራ ጊዜ የተሰጠውን የምስክርነት ቃል ፍርድ ቤቱ ሊመለከተው ይችላል፡፡

(2) ከዚህ በኃላ ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ የሚጠቅም መስሎ ከታየው የዚህ ቃል ግልባጭ ለተከሳሹ እንዲደርሰው አድርጎ በዚህ መሰረት ምስክሩ የሰጠውን ቃል ለማስተባበል ይቻላል፡፡

የአንቀጹ ርእስ እንደሚያስረዳው በፖሊስ ምርመራ የተሰጠ የምስክርነት ቃል በፍ/ቤት እንደ ማስረጃ ተደርጎ ሊወሰድ የሚቻል ስለመሆኑ በግልጽ ያስቀመጠና ጥያቄ የማያስነሳ ጉዳይ ቢሆንም መቼና በምን ዓይነት ሁኔታ ነው ይህ በምርመራ ወቅት የተሰጠ የምስክርነት ቃል በፍ/ቤት ተቀባይነት የሚኖረው የሚለውን በተመለከተ ግን ህጉ የገለጸው ነገር ባለመኖሩ ይህ አንቀጽ ለትርጉም ክፍትና እስካሁን ድረስ ገዢ የሆነ ትርጉም ያላገኘ አከራካሪ ጉዳይ ስለመሆኑ እንደሚከተለው አስረዳለሁ፡፡

የሕጉ ትርጉም

በፖሊስ ምርመራ ወቅት የተሰጠ የምስክሮች ቃልን እንደ ማስረጃ ፍ/ቤት ሊቀበለው የሚችልበት ሁኔታዎችን በምንፈትሽበት ጊዜ ሁኔታዎቹ በተለይ የተከሳሹን መብት ከመጠበቅ አኳያ ያሉትን መሰረታዊ መብቶች በጠበቀና ባከበረ መንገድ ሊተረጎሙ የሚገባ መሆን አለበት፡፡ እነዚህም ሊከበሩ የሚገባቸው የተከሳሹ መሰረታዊ መብቶች፡-

አንደኛ ህገ-መንግስታዊ ነው፡፡ ይህም ስለመሆኑ ማንኛዉም በወንጀል የተከሰሰ ሰው ያሉትን መብቶች አስመልክቶ በህገ-መንግስቱ አ.ቁ 20 ላይ የተዘረዘረ ሲሆን ከያዝነው ጉዳይ አኳያ ጠቃሚ የሚሆነው ንዑስ ቀ. 4 “የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ...”መብት ያለው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

ይህንን የህገ-መንግስት ድንጋጌ በተመለከተ ብዙ ጊዜ በፍ/ቤት ክርክር የተነሳበት በመሆኑ ( በእርግጥ ክርክር የተነሳው በሽብር እና በሙስና በተጠረጠሩ ተከሳሾች ላይ ሲሆን ምክንያቱም ዐቃቤ-ህግ ያቀረበውን ክስ ላይ አለኝ ያላቸውን ምስክሮች ለደህንነታቸው ሲባል በሚል ምክንያት ስም ዝርዝር ባለማስፈሩ የተነሳ ነው) ህገ-መንግስት ጉዳይ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የማየትና ትርጉም የመስጠት ብቸኛው ባለስልጣን የሆነው የፌዴሬሽን ምክር ቤት የተረጎመው ይህ አንቀጽ ተከሳሾች የቀረቡባቸውን ምስክሮች አስመልክቶ ያላቸው ህገ-መንግስታዊ መብት የመጠየቅ (cross-examine) ማድረግ ብቻ ስለመሆኑ አስረድቷል፡፡

የተከሳሾች ይህ የመጠየቅ መብት የሚከበረው ደግሞ ምስክሮቹ ቃላቸውን የሰጡት ተከሳሾች የመጠየቅ መብታቸው በሚከበርላቸው ፍርድ ለመስጠት በተቋቋሙ ተቋም ውስጥ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በፖሊስ በምርመራ ወቅት ምስክሮች ቃላቸውን ሲሰጡ ተጠርጣሪዎቹ የመገኘትም ሆነ የመጠየቅ መብት የላቸውም ስለዚህ የወ/ስ/ስ/ህ/ቁ 145 ልዩ ሁኔታዎች ሲተረጎሙ ይህን የተከሳሽ ህገ-መንግስታዊ የመጠየቅ መብት ያከበረ መሆን።




19ኛ ዓመት | ቁጥር 863 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ - ጥር / 29 / 2016 ዓ.ም

# ድሬዳዋ ከተማ ነጥብ ጥሏል

በብሩክ ደስታ

በ13ተኛ ሳምንት የኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ ከሀዲያሆሳዕና ጋር የተጫወተው ድሬዳዋ ከተማ በአቻ ውጤት አጠናቋል፡፡

ድሬዳዋ ከተማ በ12ተኛ ሳምንት ቅዱስ ጊዮርጊስን 3-0 ካሸነፈበት ጨዋታ የተጠቀሙበትን የጨዋታ አሰላለፍ ሳይለውጡ ወደ ሜዳ ለመግባት ችለዋል፡፡

በመጀመሪያ አጋማሽ በነበረው የጨዋታ እንቅስቃሴ ብልጫ ለመውሰድ ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የግብ ሙከራዎች ያልታዩበት ነበር፡፡

ድሬዳዋ ከተማ በቻርልስ ሙሴንጌ እና በሄኖክ አንጃው ግብ የሚሆኑ ኳሶችን ለመፍጠር ሙከራ ቢያደርጉም ግብ ማስቆጠር ግን ሲቸገሩ ነበር፡፡

በተቃራኒው ሀዲያ ሆሳዕና ተደጋጋሚ ጊዜ ሙከራ ማድረግ ቢችሉም የድሬዳዋ ከተማ ግብ ጠባቂ አብዩ ካሳዬ ማዳን ችሏል፡፡




ጨዋታው በሁለተኛው አጋማሽም በፉክክር ደረጃ እጅግ የተቀዛቀዘ አሰልቺ የጨዋታ እንቅስቃሴ የነበረ ሲሆን ሱራፌል ጌታቸው በድሬዳዋ ከተማ በኩል እንዲሁም በተመስገን ብርሃኑ እና ሰመረ ሀፍተይ አማካኝነት የግብ ዕድሎች ለመፍጠር ሙከራዎች ቢያደርጉም ስኬታማ አልነበረም፡፡

በዚህም ሙሉ የጨዋታው እንቅስቃሴ ግብ ሳያስተናግድ 0-0 በሆነ ውጤት ተጠናቋል፡፡

ከጨዋታው መጠናቀቅ በኋላ አስተያየታቸውን የሰጡት የድሬዳዋ ከተማው አሰልጣኝ ኮማንደር ሽመልስ አበበ በበኩላቸው በሁለቱም በኩል የመፈራራት ጨዋታ እንደነበር ገልጸው በቡድኑ እንቅስቃሴ ደስተኛ እንዳልነበሩ በመጠቆም ቡድኑን ከያዙ በኋላ በሁለት ጨዋታዎች አራት ነጥብ ማስመዝገባቸውን ጥሩ እንደሆነም ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

# የኢትዮጵያ የሴቶች ከ17 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድናችን ጣፋጭ ድል አስመዝግቧል



በ2024 በዶሚኒካን ሪፑብሊክ ለሚካሄደው ከ17 ዓመት በታች የሴቶች የአለም ዋንጫ ለማለፍ የኢትዮጵያ ከ17 አመት በታች የሴቶች ብሄራዊ ቡድን በሜዳው ደቡብ አፍሪካን 3 ለ 0 አሸንፏል፡፡

የኢትዮጵያ የሴቶች ከ17 አመት በታች ብሄራዊ ቡድንን የማሸነፊያ ሦስት ግቦች ህዳት ካሱ(2) እና ማናዬሽ ተስፋዬ አስቆጥረዋል፡፡

በዶሚኒካን ሪፑብሊክ በሚካሄደው የሴቶች ከ17 አመት በታች የአለም ዋንጫ አፍሪካ በሶስት ሀገራት ትወከላለች፡፡

የኢትዮጵያ ሴቶች ከ17 አመት በታች ብሄራዊ ቡድን ደቡብ አፍሪካን በድምር ውጤት ማሸነፍ ከቻሉ በ2024 በዶሚኒካን ሪፑብሊክ አዘጋጅነት በሚካሄደው የአለም ዋንጫ ቀጣይ ዙር ለማለፍ የዲሞክራትክ ኮንጎ እና ኬንያ አሸናፊ የሚገጥም ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ የሴቶች ከ17 አመት በታች ብሄራዊ ቡድን የመልሱን ጨዋታ የፊታችን ቅዳሜ የካቲት 2 በደቡብ አፍሪካ የሚያከናውን ይሆናል፡፡

# የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ወሎ !




የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን የ10ኛ ሳምንት መርሀ ግብሮች በደማቅ ሁኔታ በሳቢያን ሜዳ መከናወናቸውን ቀጥለዋል፡፡

የድሬዳዋ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጨዋታዎች በቴክኖሎጂ በማዘመን የዳኞች መነጋገሪያ መሳሪያ የተጠቀመ ሲሆን የጨዋታዎች ውጤቶችን ፍትሀዊ ለማድረግ ደግሞ 6 ዳኞችን በጨዋታው ላይ መጠቀም ጀምሯል፡፡

በ10ኛ ሳምንት የመክፈቻ ጨዋታ የሆነው የመልካ እና የአዲስ ከተማ ጨዋታ 0-0 በሆነ ውጤት መጠናቀቅ ችሏል፡፡

ጎሮ ዋልያን ሀረር ቡናን 3-2 በማሸነፍ ወሳኝ ሶስት ነጥብ ማሳካት ችሏል፡፡

ባለፉት ሁለት ተከታታይ ጨዋታዎች በአቻ ውጤት ጨዋታቸውን ያጠናቀቁት ሀፈተ ኢሳ ከ06 ህብረት ጋር 1-1 በሆነ ውጤት ሲለያዩ ሳቢያን ህብረት ቀፊራን 2-0 በሆነ ውጤት በማሸነፍ ነጥቡን ከፍ ማድረግ ችሏል፡፡

በሳምንቱ ተጠባቂ መርሀ ግብር ድሬ ካባ መስቀለኛን 1-0 እንዲሁም አኳ ድሬ ሆርሞድ በተመሳሳይ 1-0 ማሸነፍ ችለዋል፡፡

በድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን የ10ኛ ሳምንት የመጨረሻ መርሀግብር ገንደ አብዲቦሩ አሸዋን 3-2 በሆነ ውጤት በማሸነፍ ከመሪው መስቀለኛ ጋር ያለውን የነጥብ ልዩነት ወደ 2 ማጥበብ ችሏል፡፡

የድሬዳዋ ከፍተኛ ዲቪዚዮን የ11ኛ ሳምንት መርሀ ግብር የፊታችን አርብ ቅዳሜ እና እሁድ በሚደረጉ ጨዋታዎች የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡